# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ ብቃትና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት





የካቲት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ........ i

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive summary) ........ i

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አመሰራረት ........ 1

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ራእይ እና ተልዕኮ ........ 2

ራዕይ ........ 2

ተልእኮ ........ 2

ዓላማ ........ 2

የሰርቬዩ ስልጣንና ተግባር ........ 2

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 3

ሰርቬዩ የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........ 4

የዝርዝር ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 5

የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ........ 5

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria) ........ 6

በጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ ብቃትና ውጤታማነትን እንዲሁም የጂኦሳይንስ መረጃን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር ስርዓት ........ 7

ስዕላዊ መግለጫ (System Description) ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 8

ግኝቶች ........ 8

2.1. የመ/ቤቱ የማዕድን ፍለጋ ብቃት ያለው፣ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ ........ 8

ላቦራቶሪው የሚሰጠው አገልግሎት ጥራት መረጋገጡን እና በገለልተኛ አካል ግምገማ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 8

የሚከናወኑ የላቦራቶሪ ምርመራዎችና ለምርመራ ወደ ውጭ የሚላኩ ናሙናዎችን በተመለከተ፤ ........ 11

በመ/ቤቱ ላሉ የላቦራቶሪ እና የድሪሊንግ (ቁፋሮ) መሳሪያዎች የካሊብሬሽን ስራ እና የጥገና አገልግሎት መሰጠቱን በተመለከተ፤ ........ 13

ለተገልጋዮች የሚሰጡ የቁፋሮ አገልግሎት በገባው ውል መሰረት የሚፈጽም መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 16

የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ እንዲሁም የተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎች መዘጋጀታቸውን በተመለከተ፤ ........ 19

የመ/ቤቱን የናሙናዎች እና የንብረቶች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ፤ ........ 21

የኮርና የአለት ናሙናዎች አያያዝ እና አመታዊ ቆጠራ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 25

የመስሪያ ቤቱን ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም በተመለከተ፤ ........ 27

2.2. መረጃ አያያዝ፣ አሰጣጥና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር መገምገም፣..... 30

በማዕድን ስራ ከተሰማሩ ተቋማት የጂኦሳይንስ መረጃዎችን መሰብሰብን፣ በዘመናዊ መልኩ ማደራጀትን፣ ማሰራጨትና የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤...... 30

የተገልጋዮች የአገልግሎት አሰጣጥና መረጃ እርካታ ደሰሳ ጥናትና ቅሬታ አፈታትን በተመለከተ፤ ...... 32

የስልጠና አሰጣጥ ግምገማ ሥርዓትን ...... በተመለከተ፤ 33

በሥራ ላይ የሰራተኞች ደህንነት አጠባበቅን በተመለከተ ...... 35

ክፍል ሶስት ...... 37

መደምደሚያ ...... 37

ክፍል አራት ...... 39

የማሻሻያ ሃሳቦች ...... 39

አባሪ 1፡- መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria's) ...... 43

አባሪ 2፡- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ድርጅታዊ መዋቅር ...... 45

አባሪ 3፡- የዕቅድ አፈፃፀሞች ከመቶ ፐርሰንት በላይ መሆናቸውን ለማሳየት ...... 46

አባሪ 4፡ ዕቅድ አፈፃፀሞች ዝቅተኛ እና ያልተከናወኑ መሆናቸውን ለማሳየት ...... 48

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive summary)

1. በኢትዮጵያ ካለው የመልክዓ ምድር አቀማመጥ አንፃር በርካታ የማዕድን አይነቶች በተለያዩ ቦታዎች እና በተለያየ መጠን እንደሚገኙ ይገመታል፡፡ በዚህም መሰረት ሀገሪቱ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የምታደርገውን ሽግግር ለማገዝ እንዲረዳ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ማዕድናት እንዲሁም ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የስነ ምድር ጥናትና መረጃ አስመልክቶ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ለልማትና ጥናት ፕሮጀክቶች አቅርቦት በኩል የማይናቅ ድርሻ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህ ተቋም ማንኛውንም የስነ ምድር ሀብት በማጥናት መረጃዎችን ለአልሚዎች በማቅረብ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ሊሆኑ የሚችሉና የውጭ ምንዛሬን ሊያሳድጉ የሚችሉ በባህላዊ ሊለሙ የሚችሉ የተለያዩ ማዕድናት በማጥናትና መረጃውን ለአልሚዎች በማቅረብ ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለምታደርገው ጉዞ ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ መ/ቤቶች አንዱ ነው፡፡
   - መ/ቤቱ ያቋቋመው ላቦራቶሪ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራዎችን በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ ናሙናዎችን ቁጥር መቀነስ ይገባል፡፡ የተቋቋመው ላቦራቶሪ ደረጃውን ጠብቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ብቃቱ በየጊዜው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
   - ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በመ/ቤቱ ላቦራቶሪ የተለያዩ የላቦራቶሪ ዕቃዎች የተሟሉ ባለመሆናቸው፣ ሥራ ላይ ሳይውሉ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች በላቦራቶሪው መጋዘን ውስጥ የተከማቹ በመሆኑ፣ የተበላሹ የላቦራቶሪ ዕቃዎች በወቅቱ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ የማይደረግ በመሆኑ፣ በላቦራቶሪው ውስጥ አዳዲስ ማሽኖች ተገዝተው ለረጅም ጊዜ ሥራ ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ በመሆኑ ወደ ውጪ የሚላኩ ናሙናዎች መጠን እየጨመረ መምጣቱን ከማዕድን ሚኒስቴር በተገኘው ማስረጃ መሰረት ለማየት ችለናል፡፡
   - የቁፋሮ (የድሪሊንግ) እና የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡ መሳሪያዎች በትክክል አገልግሎት እንዲሰጡ በየጊዜው ካሊብሬት ሊደረጉ ይገባል፡፡ ካሊብሬሽንም ሆነ መደበኛ ጥገና ለማከናወን የሚያስችል አሰራር ስርዓት በመ/ቤቱ ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ከቀረበውና ከተከለሰው ማስረጃ መ/ቤቱ ወጥ በሆነ ሁኔታ በላቦራቶሪ ዕቃዎች ላይ የካሊብሬሽን ስራ እንደማይሰራና የቁፋሮ/ ድሪሊንግ ማሽኖች ካሊብሬት ስለመደረጋቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ አለመቅረቡ፣ እንዲሁም መደበኛ ጥገና በዕቅድ ተይዞ መከናወኑ ሲጣራ የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና እንክብካቤ ክፍል የሶስት አመት (ከ2007-2009 ዓ/ም) ዕቅድ አፈፃፀም 29%፣ 15% እና 15% መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በመ/ቤቱ የሚገኙ የቁፋሮ /ድሪሊንግ፣ እና የላቦራቶሪ ንብረቶችን በአግባቡ ለመያዝና ለመጠቀም የሚያስችል የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ያገለግሉ እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች (የቁፋሮ ማሽኖች፣ የላቦራቶሪ ማሽኖች፣ ኬሚካሎች) እና ለምርመራ የመጡ ናሙናዎች አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ ከተገልጋዮች የሚመጡ ናሙናዎች በተዝረከረከ ሁኔታ የሚቀመጡ መሆኑን፣ ምርመራቸው የተጠናቀቀ ናሙናዎች በመ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ ከ30 ዓመት በላይ ተጠራቅመው የተቀመጡ መሆኑን፣ በመካኒሳና በዋናዉ ግቢ ዉስጥ የሚገኙ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የድሪሊንግ መሳሪያዎች እንዲሁም ጥገና ቢደረግላቸው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሪጎች ሜዳ ላይ ተቀምጠው ለፀሀይና ለዝናብ በመጋለጥ ለብክነት የተዳረጉበት ሁኔታ መኖሩን፣ በተጨማሪም በ1979 ከጃፓን (የዋጋ መጠናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው) ተገዝተው የገቡ ማሽኖች እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆናቸው፣ ICP-OES (Inductively Coupled Plasma Optical Emission Spectrometry) የተባለው ማሽን ከ7 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑን፣ AAS (Atomic Absorbtion Spectrometer) የተባለ ማሽን በወቅቱ ሁለት የተገዛና አንዱ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ሁለተኛው ያለአገልግሎት ከ5 አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችለናል፡፡
- የተለያዩ የማዕድን ፍለጋ ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም መርሀ ግብር ሊዘጋጅላቸውና በመርሀ ግብሩ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የሰው ሀይል ፍልሰት በከፍተኛ ሁኔታ ያለበት መስሪያ ቤት እንደሆነ በተደጋጋሚ እንደ ችግር እየተገለጸ ባለበት ሁኔታ ዕቅዶች ከፍተኛ (ከ100%- እስከ 500% በላይ) አፈፃፀም ማሳየታቸው መ/ቤቱ ዕቅድ ሲያቅድ ጥናትን መሰረት የማያደርግ መሆኑን፣ በየአመቱ ዕቅድ ሲታቀድ የመጀመሪያውን አመት

አፈፃፀም በማየት ለቀጣዩ አመት ማሻሻያ ማድረግ የሚገባ ሲሆን በዚህ መልኩ የማይታቀድ እንዲሁም በመ/ቤቱ ዝቅተኛ አፈፃፀም የሚታይባቸው ዕቅዶች መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

- መ/ቤቱ የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዋወቅ እና በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዋወቅ እና በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት የሚያስችል መመሪያ የሌለ መሆኑን፣ በተለያዩ ተቋማት የተጠኑ የማዕድን ጥናቶች መረጃ ወደ መ/ቤቱ ወጥ በሆነ መልኩ የማይሰበሰቡ መሆኑን፣ በመ/ቤቱ የተሰበሰቡ ናሙናዎች አስፈላጊውን መረጃ አካተው ለተገልጋይ ዝግጁ ለማድረግ ቢታቀድም በእቅዱ መሰረት የማይከናወን መሆኑን፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የማይተዋወቁ መሆኑን፣ የኮርና የአለት ናሙናዎችን ደህንነት ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ ደረጃዉን የጠበቀ ጂኦሙዚየሙ በማደራጀትና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም፡-

- በመ/ቤቱ የተለያዩ ላቦራቶሪ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የተገዙ ማሽኖችና ኬሚካሎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና መጠገን የሚገባቸውንም በአፋጣኝ ጥገና እንዲደረግላቸው በማድረግ የጥራት ማረጋገጥ ስራ ሊሰራ እና ሌሎች ላቦራቶሪው ላይ መስተካከል ያለባቸውን ክፍተቶች በማስተካከል ተገቢውን ቀልጣፋ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከ10 ዓመት በፊት የተጀመረው የመ/ቤቱ ላቦራቶሪ አለምአቀፍ ዕውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ የጀመረውን ዕቅድ በፍጥነት ወደ ተግባር በማሸጋገር ወደ ውጭ የሚላኩ የማዕድን ናሙና ምርመራዎችን መጠን ሊቀነስና ለምርመራ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ የሚቀነስበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- መስሪያ ቤቱ ተግባሩን ለማከናወን የሚጠቀምባቸው የቁፋሮ (ድሪሊንግ)፣ የላቦራቶሪ እና የጂኦሳይንስ መሳሪያዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች ለብልሽት እንዳይዳረጉ ቅድመ መከላከል ሥራ ለመስራት የሚያስችል የመደበኛ ጥገና ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከልኬትና ተመሳሳይ የመለኪያ አገልግሎት የሚሰጡ

የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ የተለያዩ ማሽኖች እና መሳሪያዎች በየአመቱ ትክክል ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ካሊብሬት ሊያስደርግ ይገባል፡፡

- በመ/ቤቱ ለምርመራ የሚመጡ ናሙናዎችን በአግባቡ ለመያዝና ምርመራቸው ተከናውኖ ካለቀ በኋላም ናሙናዎቹ በባለቤቶቹ የሚወሰዱበትን የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ለረጅም አመታት የተከማቹ ናሙናዎችን የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት ጊዜያቸው በማብቃቱ ተጠግነው ስራ ላይ የማይውሉና ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ንብረቶች ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በአገር ውስጥ አይወገዱም የተባሉትን ኬሚካሎችም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሚወገዱበትን ሁኔታ በማመቻቸት እንዲወገዱ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለመወጣት እንዲስችለው የሚያዘጋጃቸውን ዕቅዶች በበቂ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ሊሆን ይገባል፡፡ ዕቅድ በሚታቀድበትም ጊዜ ያለፉ አመታትን ዕቅድ አፈፃፀም በማገናዘብና መሰረት በማድረግ የቀጣይ አመታትን ዕቅድ ሊያዘጋጅ የሚገባ ሲሆን አፈፃፀሙንም በተመለከተ በዕቅዱ መሰረት እንዲከናወን በትኩረት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ የሚያከናውናቸዉ ስራዎች ለሀገሪቱ የማዕድን ኢንቨስትመንት እድገት ወሳኝ ሚና ያለዉ በመሆኑ ለተገልጋዮች ጥራት ያለው መረጃ በተሟላ መልኩ ለማቅረብ እንዲቻል ዕቅድን መሰረት በማድረግ የስነ-ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት መሰብሰብና ማደራጀት እንዲሁም በመ/ቤቱ ያሉ መረጃዎችን መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱን መሰረት በማድረግ ማደራጀትና የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማስተዋወቅ ይገባዋል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

2. በኢትዮጵያ ካለው የመልክዓ ምድር አቀማመጥ አንፃር በርካታ የማዕድን አይነቶች በተለያዩ ቦታዎች እና በተለያየ መጠን እንደሚገኙ ይገመታል፡፡ በዚህም መሰረት ሀገሪቱ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የምታደርገውን ሽግግር ለማገዝ እንዲረዳ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ማዕድናት እንዲሁም ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የስነ ምድር ጥናትና መረጃ አስመልክቶ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ለልማትና ጥናት ፕሮጀክቶች አቅርቦት በኩል የማይናቅ ድርሻ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህ ተቋም ማንኛውንም የስነ ምድር ሀብት በማጥናት መረጃዎችን ለአልሚዎች በማቅረብ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ሊሆኑ የሚችሉና የውጭ ምንዛሬን ሊያሳድጉ የሚችሉ በባህላዊ ሊለሙ የሚችሉ የተለያዩ ማዕድናት በማጥናትና መረጃውን ለአልሚዎች በማቅረብ ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለምታደርገው ጉዞ ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ መ/ቤቶች አንዱ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አመሰራረት

3. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ማዕድን ፍለጋ ስራ በምዕራብ ኢትዮጵያ በ1890 ዓ/ም እንደተጀመረና በ1950ዎቹ መጀመሪያ የውጭና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች የማዕድን ምርመራ ስራ ማካሄዳቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የማዕድን ዘርፉን የሚከታተል መንግስታዊ ተቋም በማስፈለጉ በ1958 ዓ/ም የማዕድን ሚኒስቴር የተቋቋመ ሲሆን የማዕድን ፍለጋን በዘመናዊ መልክ ማካሄድ እንዲቻል በማዕድን ሚኒስቴር ስር ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በ1960 ዓ/ም በመምሪያ ደረጃ ተቋቋመ፡፡ መምሪያው የማዕድን ፍለጋውንና የጂኦሎጂውን ጥናት ራሱን ችሎ እንዲያከናውን በ1975 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 230/1975 "የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲቲዩት" በሚል ስያሜ ለማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር በተጠሪነት ተደራጀ፡፡ በ1992 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 194/1992 "የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ" በሚል ስያሜ ለማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኖ እንደገና ተዋቀረ፡፡

4. በ2008 ዓ.ም በተደረገው የፌደራል መ/ቤቶች አዲስ አደረጃጀት መሰረት ቀደም ሲል የያዘውን ስያሜ፣ ተግባርና ኃላፊነት እንዲያዘ ለማዕድን ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኖ እየሰራ ይገኛል፡፡

5. ሰርቬዩ በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 194/1992 መሰረት የራሱ ዓላማ፣ ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር ያሉት ሲሆን ይህንንም ለማሳካት ድርጅታዊ መዋቅር በማደራጀት እየሰራ ይገኛል፡፡

## የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ራእይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

6. በ2012 የሥነ ምድር ሽፋንን በአማካኝ ከ74.4% ወደ 100% እንዲሁም የማዕድን አለኝታ ቦታዎች ከ162 ወደ 312 ማሳደግ

### ተልእኮ

7. የሥነ-ምድር መረጃን በጥራትና በስፋት በማመንጨትና ለተጠቃሚ በማቅረብ የሃገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን

### ዓላማ

8. "በስነ-ምድር ጥናት ዘዴዎችና ስለ ምድርና በውስጧ ስለሚገኙ ማዕድናት ምርምር ማካሄድና ማናቸውንም የማዕድን ሀብት ክምችት መፈለግ፣ መመርመር እንደ አስፈላጊነቱም መገምገምና ማዕድኑ የሚገኝበትን ድንበር ለይቶ ማመልከት ነው"፡፡

## የሰርቬዩ ስልጣንና ተግባር

9. የኢትዮጲያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ሥልጣንና ተግባር ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 194/1992 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

- የጂኦሎጂ ካርታ ስራ መስራት፣ ማዘጋጀትና ማተም፣
- የአየርና የመሬት ጂኦፊዚካልና የሪሞት ሴንሲንግ ጥናት ማካሄድ፣
- የማዕድን፣ የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ፣ የጂኦተርማል፣ የሀይድሮጂኦሎጂ እና የኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ መሰረታዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በየብስልና በውሃ አካላት ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የክምችቱን መጠን መገመትና ክምችቱ የሚገኝባቸውን ሥራዎች ድንበር ለይቶ ማመልከት፣

- አላማውን ለማሳካት ባስፈለገ መጠን የእሳተ ገሞራ፣ የመሬት መቀጥቀጥ፣ የመሬት መደርመስ፣ የሚትሮራይት መውደቅና የመሳሰሉትን የተፈጥሮ ክስተቶችና ውጤቶችን የሚመለከት ጥናት ማካሄድ፣ ውጤቱንም እንደሁኔታው ለሚያስፈልጋቸው ማሳወቅ፣
- በሰርቬይ የአጭርና የረጅም ጊዜ የሰው ሀይል ፍላጎት መሰረት ሰራተኞችን ማሠልጠን
- የሥነ ምድር ሳይንስ ጥናትን በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ፣ በባለቤትነት መያዝ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ዋጋ በማስከፈል ወይም ያለክፍያ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፣ እንዲሁም መፅሔቶችም ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣
- ከስራው ጋር አግባብነት ያለውን መረጃ ሁሉ ከማንኛውም ምንጭ መጠየቅና ማግኘት
- የስነ ምድር ምርምርና ጥናትን በሚመለከት በማንኛውም ስብሰባ፡ ጉባዔና ሴሚናር ላይ መንግስትን ወክሎ መሳተፍ፣
- ከመንግስት በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣
- የንብረት ባለቤት መሆን ማስተላለፍ፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ እና ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮች ማከናወን፡፡

## የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### የሰርቬዩ ድርጅታዊ መዋቅር

10. ሰርቬዩ በዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን አንድ ዋና ጂኦሎጂስት፣ አስራ አንድ ዳይሬክቶሬቶች እና ሁለት ጽ/ቤቶች ለዋና ዳይሬክተር ተጠሪ ናቸው፡፡ ለዋና ጂኦሎጂስት ተጠሪ የሆኑ ስምንት ቴክኒካል ዳይሬክቶሬቶች ሲኖሩ በድምሩ በሰርቬዩ 19 ዳይሬክቶሬቶችና ሁለት ጽ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ (2) ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

11. ለኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ሀይል 1171 ሲሆን አሁን በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል ግን 685 ነው፡፡ ቀሪው 486 ሰራተኛ የስራ

መደብ በክፍትነት ያለ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ የሴት ሰራተኞች ብዛት 240 (35%) እና የወንድ ሰራተኞች ብዛት 445 (65%) ነው፡፡ በዚህ ወቅት ያለው የሰው ሀይል በሙያ ሲገለፅ ፒኤችዲ ወንድ 1፣ ማስተርስ ዲግሪ ወንድ 25 (4%) ሴት 8 (1%) ድምር 33፣ ቢኤ ዲግሪ ወንድ 150 (22%) ሴት 75 (11%) ድምር 225፣ ዲፕሎማ ወንድ 68 (10%) ሴት 59 (9%) ድምር 127 እና ከዲፕሎማ በታች ወንድ 201 (29%) እና ሴት 98 (14%) በድምሩ 299 በጠቅላላው 685 ሠራተኞች በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ይገኛሉ፡፡

## ሰርቬዩ የፋይናንስ ምንጭ

12. የኢትዮጵያ ጆኦሎጂካል ሰርቬይ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት ከሚሰጥ ድጎማ፣ ሰርቬዩ ከሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋና ሌሎች ክፍያዎች ከሚገኝ ገንዘብ በጀት የሚጠቀም ሲሆን ከ2007-2009 በጀት ዓመት የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 165,040,596.00 | 132,191,419.61 | 80% |
| 2008 | 111,116,290.00 | 103,873,084.09 | 93% |
| 2009 | 152,973,400.00 | 128,358,360.00 | 84% |

## የኦዲቱ ዓላማ

13. ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን፣ በዓለም ዓቀፍ የክዋኔ ኦዲት ስታንደርድ እንዲሁም በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል መሰረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ ብቃትና ውጤታማነት መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## የዝርዝር ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

14. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የሚሸፍነው ከ2007 እስከ 2009 ያሉትን ሶስት አመታት ሲሆን ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን በመከለስ፣ በናሙና ከተመረጡ የክልልና የፌዴራል ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች እንዲሁም ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ በሰርቬዩ ያሉ የድሪሊንግ እና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች መጋዘኖችን እና ላቦራቶሪዎችን በአካል በማየትና ተያያዥ መረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከድሪሊንግ ዳይሬክቶሬት፣ በጂኦኬሚካል እንዲሁም በሚኒራሎጂና ጂኦቴክኒካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬቶች፣ ከጂኦሳይንስ መረጃ ዳይሬክቶሬት፣ ከማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት ዳይሬክቶሬት፣ ከሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስናና ጥገና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት፣ ከኦሮሚያ ማዕድን፣ ኢነርጂና ዉሃ ቢሮ፣ ከኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስትቲዩት፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አክርዲቴሽን ጽ/ቤት፣ ከክሪፕቶ ማይኒንግ (Kripto Mining) እና ከከፊ ሚነራልስ ኢትዮጵያ ሊሚትድ (Kefi Minerals Ethiopia Ltd) ከላይ በተጠቀሱት የኦዲት ዘዴ ማስረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

15. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ **የማዕድን ፍለጋ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ** እየተከናወነ መሆኑን መገምገም ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች

### የኢዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

16. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም-

1. የማዕድን ፍለጋ ብቃት ያለው ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
2. መረጃ አያያዝ፣ አሰጣጥና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር መገምገም፤

ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)

17. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን (Audit Issues) ለመመዘን የሚረዱ 23 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት የሰርቬዩ መቋቋሚያ አዋጅ፣ የማዕድን ፍለጋ ክምችትና ግምት፣ የድሪሊንግ አገልግሎት፣ ጂኦሳይንስ መረጃ አገልግሎት፣ የጂኦኬሚካል ላቦራቶሪ እና የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና ክብካቤ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቶች፣ የ5 አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ እንዲሁም መልካም የሥራ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁት መመዘኛ መስፍርቶች ላይ መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም **በአባሪ 1** ተያይዘዋል፡፡


# በጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ ብቃትና ውጤታማነትን እንዲሁም የጂኦሳይንስ መረጃን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር ስርዓት

## ስዕላዊ መግለጫ (System Description)

1.




2.



# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1. የመ/ቤቱ የማዕድን ፍለጋ ብቃት ያለው፣ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

**ላቦራቶሪው የሚሰጠው አገልግሎት ጥራት መረጋገጡን እና በገለልተኛ አካል ግምገማ መደረጉን በተመለከተ፤**

18. ላቦራቶሪ የሚሰጠው አገልግሎት የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ያሟላ እንዲሆን በየደረጃው የጥራት ቁጥጥር ሊኖር እና በእያንዳንዱ የላቦራቶሪ ምርመራ ደረጃ ላይ በመረመረው አካል/ባለሙያ ማረጋገጫ ሊሰጥ እንዲሁም የላቦራቶሪ አገልግሎት በገለልተኛ አካል ሊገመገም ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ

- ለጂኦኬሚካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡን ምላሽ እንዲሁም ሪፖርቱን በማየት ለመረዳት እንደተቻለው የላቦራቶሪ ውጤት ጥራት ቁጥጥር ላይ የሚያረጋግጠው አንድ ባለሙያ ብቻ መሆኑ
- ለጂኦኬሚካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡን ምላሽ ጥራት ቁጥጥር ላይ የተዘረጋው አደረጃጀት (Flat) የሆነ ስትራክቸር ያለው በመሆኑ ጥራቱ ላይ በደረጃው የሚገመገምበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

- መ/ቤቱ ከ2003-2007 ዓ.ም እና ከ2008-2012 ዓ.ም ባዘጋጀዉ የመ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ የISO ስታንዳርድ ዕዉቅና እንዲኖረዉ ለማድረግ እና ለተገልጋዮች የሚሰጠውን የላቦራቶሪ አገልግሎት ጥራት ያለው ለማድረግ ዕቅድ የተቀመጠ ቢሆንም፡-
    - የሶስቱን አመታት ማለትም የ2007፣ የ2008 እና የ2009 አፈፃፀም ለማየት እና ለመረዳት እንደተቻለው መ/ቤቱ በወርቅና ቤዝ ሜታልስ ምርመራ አይነት የISO-17025 ዕውቅና እንዲሰጠው ለኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት ማመልከቻ ማስገባት እንዲሁም የብቃት ግምገማ ተከናውኖ የተሰጠውን ግብረ መልስ መሰረት በማድረግ ማስተካከያ እርምጃዎችን

በመውሰድ የISO-17025 ዕውቅና ማግኘትን 100% ማከናወን በሚል የታቀደ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑን፣

- ማስረጃ በመከለስ እና ከቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለው ላቦራቶሪው የISO 17025 እውቅና እንዲያገኝ የሚያስችለው XRF ማሽን ባለመኖሩ ተገልጋዮች ናሙናዎችን ለማስመርመር ወደ ዉጭ የሚልኩ መሆኑን እንዲሁም መ/ቤቱ ይህንን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል ግዥ ለማከናወን የሄደበት መንገድ ቢኖርም መ/ቤቱ ላይ በታዩ ክፍተቶች ለሶስት አመታት ግዥው ያልተከናወነ መሆኑን፣
- ለሁለት አመታት ግዥው በውስን ጨረታ አለመሳካቱ እየታወቀ ለሶስተኛ ጊዜ ይኸው ማሽን በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲከናወን የተጠየቀበት ሁኔታ መኖሩን፣
- በጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ ውስጥ በናሙና ምርመራ ውጤት ጥራት እንዳይኖር እና ላቦራቶሪው የISO-17025 ዕውቅና እንዳይሰጠው ያደረጉ የተለያዩ የአሰራር ክፍተቶች እንዳሉ ከእነዚህም ውስጥ ጥሬ ዕቃ አለመሟላት፣ የማስረጃዎች (ዶክመንት) አያያዝ ችግር፣ የማያገለግሉ ኬሚካሎችን እና መሳሪያዎችን አለማስወገድ፣ ጥራታቸውን ያልጠበቁ ኬሚካሎች የሚገዙ መሆናቸው፣ መሳሪያዎች አገልግሎት በመስጠት ብዙ የቆዩ መሆናቸው፣ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች ለምርመራ አገልግሎት የሚውሉ መሆኑ፣ ግብአት አቅርቦት እጥረት ለምሳሌ ሰርቲፋይድ ሪፈረንስ ማቴሪያል (CRM) እንዲሁም ብቃት ያለው ባለሙያ በላቦራቶሪው አለመኖሩ እና ለካሊብሬሽን ምቹ ሁኔታ አለመፈጠር መሆናቸውን ከክፍሉ ኃላፊዎች መገለጹን፣
- በሚኒራሎጂና ጂኦቴክኒካል ክፍል ውስጥ የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ አለመኖሩን እንዲሁም በኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ፅ/ቤት እ.ኤ.አ በ2012 ከተደረገው የላቦራቶሪ ግምገማ በቀር በውጭ አካል የተደረገ ግምገማ አለመኖሩ ከቃለ መጠይቅ መረዳት መቻሉ፣
- የኢትዮጵያ አክርዲቴሽን ጽ/ቤት የመ/ቤቱ የላቦራቶሪ ምርመራ ዉጤትን ጥራት ለማረጋገጥ የሚተገብራቸዉ ፖለሲዎች፣ ሲስተሞች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮሲጀሮች እና ትእዛዞች በሚመለከተዉ አካል ያልፀደቁና ዶክመንትድ ያልሆኑ መሆናቸዉን በጥቅምት 2012 መ/ቤቱ የአሰራር ግምገማ ባደረገበት ወቅት መግለፁን

በኦዲት ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡

20. ስለሁኔታው የመቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

- ላቦራቶሪው የሚያወጣቸው ሪፖርቶች ላይ የክፍሉ አስተባባሪዎች ጥራቱን ካረጋገጡ በኋላ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያው በተጨማሪ የጥራት ቁጥጥር ስራ በመስራት ካረጋገጠ በኋላ የሚፈርም መሆኑን፣ የተጠቀሰው የXRF ማሽን ግዥ በሂደት ላይ መሆኑን በተለይ በአሁኑ ጊዜ ለሶስተኛ ጊዜ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ለመፈፀም ሂደቱ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን፣ መ/ቤቱ መመሪያ፣ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) እና ስታንዳርድ እንደሚጠቀም በተጨማሪም በቅርቡ የላቦራቶሪ 26 የQuality Mannual በበላይ ኃላፊው የጸደቀ እና በዚሁ መሰረት እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ መሆኑን ሌሎች የሚቀሩ ካሉ የሚፀድቁ መሆኑን፣
- አጠቃላይ ስለላቦራቶሪው የተገለፀው የተወሳሰበ ችግር ትክክል እንደሆነና ISO አክሪዲቴሽን ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ላይም እንቅፋት በመፈጠሩና ይህንን በየደረጃው ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

21. ኃላፊዎች ከላይ የተጠቀሰውን ምላሽ ቢሰጡም ጥራት የሚረጋገጠው አንድ ባለሙያ መሆኑ በራሱ በሪፖርት ጥራት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያለው በመሆኑ፣ የXRF ማሽን ግዥ ለማከናወን ሁለት ጊዜ ግዥው ሲቋረጥ የመ/ቤቱ ክፍተት በመሆኑ እንዲሁም ለሶስተኛ ጊዜም ይህንኑ የግዥ ዘዴ ለመጠቀም መሞከሩ እና የተሻለ አማራጭ በመፈለግ ግዥው ፈጣን እንዲሆን አለማድረጉ እና የISO ዕውቅና ለማግኘት የታቀደው ከ10 ዓመት በፊት ሆኖ ሳለ እስካሁን ተፈጻሚ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንዳለ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

22. በእያንዳንዱ የምርመራ ደረጃ ላይ በሚመለከተው አካል/ባለሙያ ጥራቱ እንዲረጋገጥና ጥራት ቁጥጥሩ ጠንካራ እንዲሆን ባለመደረጉ፣ በላቦራቶሪው ላይ ያሉና በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱ የተለያዩ ክፍተቶች እንዲወገዱ አለመደረጉ የናሙና ውጤት ጥራት ላይ ከፍተኛ ችግር እንዲኖረው፣ በተገልጋዮች ተአማኝነትን እንዲያጣ እና ያለዉ ተቀባይነት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

የሚከናወኑ የላቦራቶሪ ምርመራዎችና ለምርመራ ወደ ውጭ የሚላኩ ናሙናዎችን በተመለከተ፤

23. መ/ቤቱ ያቋቋመው ላቦራቶሪ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራዎችን በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ በማድረግ ወደ ውጪ የሚላኩ ናሙናዎችን ቁጥር መቀነስ ይገባል፡፡ የተቋቋመው ላቦራቶሪ ደረጃውን ጠብቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ብቃቱ በየጊዜው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ በመ/ቤቱ ላቦራቶሪ፣

- የተለያዩ የላቦራቶሪ ዕቃዎች የተሟሉ ባለመሆናቸው፣
- ሥራ ላይ ሳይውሉ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ በመሆኑ፣
- የተበላሹ የላቦራቶሪ ዕቃዎች በወቅቱ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ የማይደረግ በመሆኑ፣
- አዳዲስ ማሽኖች ተገዝተው ለረጅም ጊዜ ሥራ ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ በመሆኑ፣

ወደ ውጪ የሚላኩ ናሙናዎች መጠን እየጨመረ መምጣቱን ከማዕድን ሚኒስቴር በተገኘው ማስረጃ መሰረት ለመረዳት ችለናል፡፡

- ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኘ ማስረጃ እንደሚያሳየው ከ2007 እስከ 2009 ዓ/ም ባሉት ሶስት አመታት ውስጥ ከማዕድን ፈቃድና አስተዳደር በቁጥር 757 የሚደርሱ እና 317,279.96 ኪ.ግ የሚመዝኑ፣ ከገበያ ልማት ትስስርና ትንበያ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 293 የሚደርሱ እና 725.7 ኪ.ግ. የሚመዝኑ በድምሩ በቁጥር 1050 ሚደርሱ እና 318,005.66 ኪ.ግ. የሚመዝኑ የተለያዩ የናሙና አይነቶች ከተለያዩ ድርጅቶች ወደተለያዩ ሀገሮች ለማስመርመር የተጠየቁ እና የተላኩ መሆናቸውን፣
- በመ/ቤቱ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት የመዘግየት ሁኔታ እንዳለ እና በዚሁ የተነሳ ወደ ውጭ በመላክ ለማስመርመር እንዲቻል ወደ ማዕድን ሚኒስቴር የሄዱበት ሁኔታ መኖሩን ተገልጋዮች መግለፃቸውን

በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

25. ስለጉዳዩ ለሚኒራሎጂና ጂኦቴክኒካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ወደ ውጭ ስለሚላኩ ናሙናዎች መረጃ እንደሌላቸው ነገር ግን X-

Ray Diffraction (XRD) ማሽን በመበላሸቱ ለምርመራ ወደ ላቦራቶሪው የመጡ ናሙናዎች የተመለሱበት ሁኔታ እንዳለ እና ይህ ማሽን ከ2 ዓመት በላይ ሳይጠገን እንደተቀመጠ የገለፁ ሲሆን ለጂኦኬሚካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ X-Ray Florucence (XRF) የሚባል የላቦራቶሪ ማሽን ከተበላሸ 3 ዓመት እንደሆነው እና በዚህም ምክንያት እንደታንታለም ያሉ ማዕድናት በማዕድን ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ፈቃድ ሲያገኙ ወደ ውጭ ተልከው የሚመረመሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

26. ስለሁኔታዉ መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ተጠይቀው

- ናሙናዎች ወደ ውጭ ይላኩ አይላኩ ለማለት ይህ ተግባርና ሀላፊነት የመ/ቤቱ አለመሆኑን፣
- X-Ray Diffraction (XRD) እና X-Ray Florucence (XRF) የተባሉ ማሽኖችን በተመለከተ የተገኘው ትክክል መሆኑን እና ይህን ችግር ለመፍታት X-Ray Diffraction (XRD) ለማስጠገን በባንክ ኤልሲ ተከፍቶ በዉጭ ምንዛሬ እጥረት የተፈቀደ አለመሆኑ ለዚህም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣
- X-Ray Florucence (XRF) ማሽንን በተመለከተ በአዲስ ለመተካት በሂደት ላይ መሆናቸውን
- ናሙናዎች ለመጥቀስ ታንታለም ለምርመራ ወደ ውጭ የሚላኩት ላቦራቶሪው የISO-17025 ዕውቅና ባለማግኘቱ ሳይሆን የXRF ማሽን በመበላሸቱ መሆኑን እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠ አቅጣጫ መሰረት ላቦራቶሪው ዕውቅና ለማግኘት ትኩረት ሰጥቶ እየተሰራባቸው ያሉት ወርቅና ቤዝ ሜታሎች ላይ መሆኑን እና ዕውቅናውን ባለመገኘቱ ምክንያት ወርቅና ቤዝ ሜታሎች ወደ ውጭ ለምርመራ እየሄዱ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን፣
- በመ/ቤቱ ከፍተኛ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍልሰት ያለ በመሆኑ እና በአሁኑ ወቅት በጀማሪ ባለሙያዎች ስራዎች የሚሰሩ መሆኑን

በቀረበላቸዉ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባው ወቅት እና በረቀቅ ሪፖርት ላይ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

27. የመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ወደ ውጭ የሚላኩ ናሙናዎችን በተመለከተ የመ/ቤቱ ተግባርና ሀላፊነት እንዳልሆነ ቢገልጹም ያሉትን መሣሪያዎያች ወቅታዊ ጥገና በማድረግ በመ/ቤቱ ላቦራቶሪ ሊመረመሩ የሚችሉ ናሙናዎችን ለመቀነስ የራሱን

ድርሻ መወጣት ይችል ስለነበረ እና ችግሩ የመ/ቤቱም እንደሆነ የሚያስማማ በመሆኑ ምላሹን ሙሉ ለሙሉ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

28. ላቦራቶሪው የጥራት ማረጋገጫውን ባለማግኘቱ እና ለመሳሪያዎች ወቅታዊ ጥገና በማድረግ ጥራት ያለውና አስተማማኝ አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑ የተለያዩ ናሙናዎች ወደ ውጪ መላክ እንዲቀንስ የራሱን ድርሻ አለመወጣቱ ሀገሪቱ ማግኘት ያለባትን ገቢ እንዳታገኝ እና ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ ያደርጋል፡፡

**በመ/ቤቱ ላሉ የላቦራቶሪ እና የድሪሊንግ (ቁፋሮ) መሳሪያዎች የካሊብሬሽን ስራ እና የጥገና አገልግሎት መሰጠቱን በተመለከተ፤**

29. የቁፋሮ (የድሪሊንግ) እና የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡ መሳሪያዎች በትክክል አገልግሎት እንዲሰጡ በየጊዜው ካሊብሬት ሊደረጉ ይገባል፡፡ ካሊብሬሽንም ሆነ መደበኛ ጥገና ለማከናወን የሚያስችል አሰራር ስርዓት በመ/ቤቱ ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ፡-

- በቀረበልን ማስረጃ መሰረት በላቦራቶሪ ላይ ካሊብሬሽን የተከናወነው በትግራይ ክልል ብቻ በሚገኙ የመ/ቤቱ ወርቅ ሚዛኖች ላይ ሲሆን በላቦራቶሪው ውስጥ ያሉት ማሽኖችና የናሙና ማድረቂያ ማሽን ካሊብሬት ያልተደረጉ መሆኑ፣ የቁፋሮ/ ድሪሊንግ ማሽኖች ካሊብሬት ስለመደረጋቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- የማዕድን መቆፈርያ መሳሪያዎች ረጅም ጊዜ ያገለገሉ መሆናቸው እና የሞተር እድሳት ተደርጎላቸው ስለማያውቅ አስፈላጊውን የቁፋሮ ልኬት (ፓራ ሜትር) በመጠቀም ቁፋሮ ለማካሄድ እንዳልተቻለ እና ይህ ችግር አሁንም ድረስ ያልተቃለለ መሆኑ፣
- ብሔራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት በሰራው የካሊብሬሽን ስራ ላይ መ/ቤቱ ማስተካከያ እየሰራ እንዲሄድ በዕቃው ላይ ያለውን ክፍተት በሰርተፍኬት ላይ መዝግቦ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ በሰጠው የማስተካከያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- በአብዛኛው መ/ቤቶች ማሽኖችን ካሊብሬት ለማስደረግ የሚመጡት አስገዳጅ ሁኔታ ሲመጣ እንጂ በመርሀ ግብር መሰረት አለመሆኑን የብሔራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት የስራ ሃላፊዎች መግለፃቸው፣

በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

- የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና እንክብካቤ ክፍል ላይ መደበኛ ጥገና ዕቅድ ተይዞ ስለመከናወኑ የማጣራት ስራ በተሰራበት ወቅት የሶስት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ከታች የተገለፀውን ያሳያል፡-
    - በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የመሳሪያዎች የቅድመ ብልሽት ጥገና በቁጥር 70 ለማከናወን ቢታቀድም በቁጥር 20 (29%) የተከናወነ መሆኑን፣
    - በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የመሳሪያዎች ቅድመ ብልሽት ጥገናና እንክብካቤ በቁጥር 80 ማከናወን ተብሎ ቢታቀድም በቁጥር 12 (15%) የተከናወነ መሆኑን፣
    - በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የመሳሪያዎች የቅድመ ብልሽት ጥገና በቁጥር 80 ለማከናወን ቢታቀድም በቁጥር 9 (15%) የተከናወነ መሆኑን፣
- ለቁፋሮ /ድሪሊንግ አገልግሎት ተጠግነው ስራ ላይ መዋል እና ለመ/ቤቱ ከፍተኛ ጥቅም ሊኖራቸው የሚችሉ በቁጥር ወደ ስምንት የሚደርሱ የቁፋሮ መሣሪያዎች /ሪግ/ ለዝናብና ፀሀይ በተጋለጠ ሁኔታ መካኒሳ በሚገኘው የመ/ቤቱ ግቢ ውስጥ የቆሙ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

31. ስለሁኔታዉ የመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ተጠይቀው
    - አንዳንድ መሳሪያዎች በሃገር ዉስጥ ካሊብሬት ሊደረጉ የማይችሉ መሆኑን፣
    - በትግራይ ክልል ብቻ በሚገኙ የወርቅ ሚዛኖች ላይ ካሊብሬሽን መሰራቱ ትክክል ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን በሌሎች ክልሎች ያሉ ሚዛኖች ካሊብሬት የተደረጉበት ሁኔታ እንዳለ እና ሰርትፊኬት በቀጣይ የሚሰጥ መሆኑን፣
    - መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸው የድሪሊንግ መሳሪያዎች ከ30 ዓመት በላይ ያገለገሉ በመሆናቸው መሳሪያዎቹን የሰራቸው ፋብሪካ የተዘጋ በመሆኑ ካሊብሬት አለመደረጋቸውን እና ከብሄራዊ ስነ ልክ ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ በመሆን ለመስራት ክትትል የሚደረግ መሆኑን

- የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና ጥገናና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዕቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነዉ በሰው ሃይል እጥረት ሲሆን 5 ሰራተኛ በመልቀቁ እና በፊት የነበረው የስራ ሁኔታ ችግር የነበረበት በመሆኑ መሆኑን፣
- በቁጥር 8 የሚደርሱ ሪጎችን በተመለከተ የጥገና ስፍራው መካኒሳ ሲሆን ለጥገና ሲባል ተሸፍነው የነበሩ ሽራዎች ተነስተው የነበሩ ሲሆን ጥገናው በመጠናቀቁ በአሁኑ ወቅት ሽራው ተሸፍኖ የሚገኝና በቀጣይ መጠለያ ለመስራት የሚታሰብበት መሆኑን፣
- በሚኒራሎጂና ጂኦቴክኒካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሚገኙ ተደጋጋሚ ጥገና ተደርጎላቸው የማይሰሩ ኮምፕረሰሮች እና ኮምፒቴሽን ስትሬንግዝን ማሽኖች ውጭ ሀገር ድረስ ለማስጠገን ተሞክሮ ያልተቻለበት ሁኔታ በመኖሩ በቀጣይ ሊወገዱ እንደሚገባ ሲሆን በጥገና ላይ ያሉ እና የተጠገኑ መኖራቸዉን፣ AAS (Atomic Absorbtion spectrometer) በኦዲቱ ወቅት በጥገና ላይ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ተጠግኖ ስራ ላይ የዋለ መሆኑን፣
- በላቦራቶሪ ዕቃ ግምጃ ቤት የተለያዩ ማሽኖች ተጠግነዉ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ መሆን አለመሆናቸዉ በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተቀመጡ ቢኖሩም በቀጣይ የሚጠገኑትን መጠገን እንዳለባቸዉና የማይጠገኑት ማስወገድ እንደሚገባ የተያዘ አቅጣጫ መኖሩን፣

በቀረበላቸዉ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

32. የመ/ቤቱ የስራ ሀላፊዎች በትግራይ ክልል ከተሰራው የወርቅ ሚዛኖች የካሊብሬሽን ስራ ውጭ ሌላ የተሰራ የካሊብሬሽን ሥራ አለ ቢሉም ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

33. የቁፋሮ (የድሪሊንግ) እና የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡ ዕቃዎች ተጠግነው በአስቸኳይ ወደ ስራ እንዲገቡ የሚያስችል መደበኛና ወጥነት ያለው የጥገና እና የካሊብሬሽን ስራ አለመኖሩ በመ/ቤቱ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ የራሱን ተፅዕኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በላይ የሚታቀዱ እቅዶች ባልተጠገኑ ማሽኖች ምክንያት ዝቅተኛ አፈፃፀም እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ማሽኖች ወቅታዊ ጥገና ባለማግኘት ያለስራ እንዲቀመጡ እና የመ/ቤቱ ሀብት እንዲባክን ያደርጋል፡፡

**ለተገልጋዮች የሚሰጡ የቁፋሮ አገልግሎት በገባው ውል መሰረት የሚፈጽም መሆኑን በተመለከተ፤**

34. ለተገልጋዮች የሚሰጠው የቁፋሮ (የድሪሊንግ) አገልግሎት ከተገልጋዮች ጋር በተገባው ውል መሰረት የሚተገበርበት የአገልግሎት የአሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ለተገልጋዮች የድሪሊንግ አገልግሎት ለመስጠት ውል ከተዋዋለ በኋላ በተዋዋለው መሰረት ጨርሶ የማያስረክብ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን የአፈፃፀም ክፍተቶች ማየት ችለናል፡-

- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከሎዝ ቤዝ ሀ/የተ/የግ/ማህበር ጋር እ.አ.አ ግንቦት 22/2017 (ግንቦት 30/2009 ዓ/ም) ውል የተዋዋለ ሲሆን ምንም ስራ ባልተሰራበት ሁኔታ ከውሉ ቀን አንስቶ ስራው እስከተጀመረበት ሀምሌ 15/2009 ዓ/ም ድረስ የ75 ቀናት መዘግየት ከመኖሩም በላይ በነዚህ ቀናት ውስጥ ለአስራ አንድ ሰራተኞች ምንም እንኳን መስክ ላይ ቢሆኑም የውሎ አበል እና የምግብ ድጎማ ቶፕ አፕ ክፍያ ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀናት ሲከፈላቸው የቆየ መሆኑ እና አጠቃላይ የገንዘብ መጠኑን ለማወቅ የተደራጀ መረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣ በተጨማሪም ስራው በ30 የሥራ ቀናት እንዲያልቅ የሚል ቢሆንም ስራው ከተጀመረበት ሀምሌ 15/2009 ዓ/ም እስከተጠናቀቀበት መስከረም 5/2010 ዓ/ም ድረስ 10 የሚሆኑ የስራ ቀናት የዘገየ ሲሆን በአጠቃላይ የ85 ቀናት መዘግየት መታየቱን፣
- ከኢትዮጵያ አይረን ኤንድ ስቲል ፋብሪካ ጋር በአማራ ክልል ዋግ ህምራ ዞን ዝቋላ እና ሳኽል ወረዳ ላይ ቁፋሮ ለማድረግ በየካቲት 16/2009 ዓ/ም ውል የተዋዋለ ሲሆን ስራ ሳይጀመር ከውሉ አንድ ወር ከሀያ አንድ ቀን በመዘግየት የጀመረ መሆኑን፣
- መ/ቤቱ ከደርባ ሚድሮክ ጋር የቁፋሮ /ድሪሊንግ/ አገልግሎት ለመስጠት እ.አ.አ. በየካቲት 28/2017 (የካቲት 20/2009 ዓ/ም) በ55 ቀናት ውስጥ ስራው እንዲጠናቀቅ ውል የተዋዋሉ እና የመጀመሪያው ውል እንደተጠናቀቀ ስራው ሳይቋረጥ ለተጨማሪ አንድ ወር (30 ቀን) የተዋዋሉ ሲሆን በአጠቃላይ ሁለቱ ውሎች በ85 ቀናት ውስጥ ማለትም ግንቦት 15/2009 መጠናቀቅ ያለባቸው ሆኖ ሳለ ሐምሌ 27/2009 በመጠናቀቁ የ75 ቀን መዘግየት መኖሩን፣

- በሱሉልታ ከሚገኘው የመለስ ፋዉንዴሽን ህንፃ ግንባታ ጋር በ20 ቀን የሚጠናቀቅ በጂኦቴክኒክ እና በድሪሊንግ የታገዘ አፈር ምርመራ ለማድረግ እ.አ.አ. በመጋቢት 16/2016 (መጋቢት 8/2008 ዓ/ም) ውል የገባ ሲሆን የመስክ ስራ በግንቦት 8/2008 በመጠናቀቁ አንድ ወር ከ10 ቀናት መዘግየት መኖሩን፣
- በጎንደር መገጭ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክት ላይ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የውሃ መሰረት ልማት ኮንስትራክሽን ዘርፍ ጋር እ.አ.አ በመጋቢት 17/2016 ዉል የገባ ሲሆን በውሉ መሰረት ስራው በ159 ቀን መስከረም 19/2009 መጠናቀቅ የነበረበት ሲሆን 60 ቀን ዘግይቶ በህዳር 19/2009 ውሉ መቋረጡ መገለፁ እና ድርጅቱ ውሉን በማቋረጡ የከፈለው ካሳ ክፍያ ማስረጃ አለመቅረቡን፣
- በጋምቤላ ክልል ባሮ ወንዝ አካባቢ የጂኦቴክኒክ ቁፋሮ ስራ ለመስራት በ130 የስራ ቀናት እንዲጠናቀቅ እ.አ.አ. መጋቢት 8/2016 (የካቲት 30/2008 ዓ/ም) ውል የፈፀመ ሲሆን በውሉ መሰረት ስራው መጠናቀቅ ካለበት ወቅት ዘግይቶ መ/ቤቱ በቀን 06/11/2008 ለድርጅቱ ስራው እንዲቋረጥ ደብዳቤ የፃፈና በቀጣይ ስራው በምን መልኩ እንደቀጠለ በግልፅ የሚያስረዳ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉን፣
- በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በመልካ ሶዳ ወረዳ ልዩ ስሙ አኮቴ በሚባል አካባቢ መ/ቤቱ ከብሄራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኩባንያ ጋር በግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ.ም የ5000 ሜትር የጉድጓድ የቁፋሮ የውል ስምምነት ያደረገ ቢሆንም ስራው የተጀመረው ነሐሴ 18/2007 ዓ.ም መሆኑን እና ውል ከተገባበት 81 ቀናት ዘግይቶ የተጀመረ መሆኑን፣ በውሉ መሰረት ስራው ተጀምሮ ቢሆን ሕዳር 15 ቀን 2008 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ቢሆንም እስከ በጥር 27 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ እየተሰራ የቆየና በዚህ መሀል ግጭት የተፈጠረ መሆኑን፣ ስራው በውሉ መሰረት ባለመጀመሩ ስራው ባልተጠናቀቀበት ሁኔታ ግጭት እስከተፈጠረበት ወቅት 40 ቀን ልዩነት መኖሩን በአጠቃላይ ስራው ባልተጠናቀቀበት ሁኔታ የ121 ቀናት መዘግየት እንደተፈጠረ እና የአኮቴ የቁፋሮ ስራ በውል መሰረት ባለመከናወኑ 45,000,000.00 (አርባ አምስት ሚሊየን ብር) የሚያወጡ የመ/ቤቱ ንብረቶች ማለትም አንድ የውሃ ቦቴ እና ሁለት የመቆፈርያ መሳሪያዎች ተቃጥለው ከጥቅም ውጪ መሆናቸዉን፣

- መ/ቤቱ በመደበኛነት ማውጣት ካለበት ወጪ በተለየ ውል ባለማክበሩ ምክንያት በተጨማሪነት የተከሰቱ ወጪዎችን ዝርዝር ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ወቅት ድረስ ግልፅ የሆነ መረጃ አለመቅረቡን፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

36. ስለሁኔታዉ መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀዉ

- የተሰጠው አስተያየት ትክክል እንደሆነ እና የውል ግዴታቸውን ባልተወጡት ህጋዊ እርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ፣
- ከሎዝ ቤዝ ሃ/ተ/ግ/ማ፣ ከኢትዮጵያ አይረን ኤንደ ስቲል ፋብሪካ፣ ከደርባ ሜድሮክ፣ በጋምቤላ ክልል ባሮ ወንዝ አካባቢ የጂቴክኒክ ቁፋሮ እና ኦኮቴ አካባቢ ከብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኩባንያ ጋር የተደረጉ ስምምነቶች የዘገዩት በዋናነት የቁፋሮ ሳይቶች ዝግጅት በድርጅቶች በኩል ጊዜ በመዉሰዱ፣ የድሪሊንግ ማሽን ብልሽት እና የፀጥታ ችግር በማጋጠሙ እና እነዚህ ችግሮች የጋራ በመሆናቸዉ እንዲሁም ድርጅቶች በመስክ ለሚሰሩ ሰዎች ስራዉን ካስጀመሩ ጀምሮ በስምምነቱ መሰረት አበል ሲከፍሉ በመቆየታቸዉ ስራዉ በታሰበለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ የካሳ ክፍያ የሚያስኬድ ባለመሆኑ የተከፈለ የካሳ ክፍያ አለመኖሩን፣
- ከውል በኋላ ቅድመ ክፍያውን አሰሪው ከፍሎ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ግዥ የሚካሄድ በመሆኑ፣ ወደ ሳይት በሚደረገው እንቅስቃሴ የጭነት መኪና ብልሽት የሚያጋጥም በመሆኑ፣ የቁፋሮ ሳይቶችና መንገዶች በሚፈለገው ሁኔታ የማይስተካከሉ በመሆኑ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች አርሶ አደሮች በበዓል አትስሩብን የሚሉ በመሆኑ፣ በቁፋሮ ስራ ላይ የመሳሪያዎች (የሪግ) ብልሽት የሚያጋጥም በመሆኑ፣ በቁፋሮ ሳይት ላይ የአለት ጥንካሬ የሚያጋጥም በመሆኑ እንዲሁም በተፈጥሮ ሁኔታ ለምሳሌ ከባድ ዝናብና ጭቃ በሚኖር ወቅት በቀላሉ የማያንቀሳቅስ በመሆኑ የቁፋሮ ስራ ውል የሚዘገዩበት ሁኔታ መኖሩን፣

በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርት ላይ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

37. ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም የመሳሪያ ብልሽት ሲያጋጥም በፍጥነት ጥገና በማድረግ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ፣ ቅድመ መስክ ዝግጅት ስራው ከመጀመሩ

በፊት መጠናቀቅ ያለበት በመሆኑ፣ ውሉ ላይ በተገለፀዉ መልኩ በድርጅቱ ላይ ቅጣት ሊጣል የሚገባው በመሆኑ፣ ሥራው በመጓተቱ መ/ቤቱ ተጨማሪ ወጪ ለማውጣት በመዳረጉና ስራ በማይሰራበት ሁኔታ ለሰራተኞች ከወር በላይ ለሚሆን ጊዜ አበል መክፈል አግባብ ባለመሆኑ የተሰጠዉን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

38. ለተገልጋዮች የሚሰጠው የቁፋሮ (የድሪሊንግ) አገልግሎት በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት ባለመከናወኑና በገባው ውል መሰረት ሥራውን ባለመስራቱ ለአላፈላጊ ወጪዎች ከመዳረጉም በላይ ከፍተኛ የሆነ የንብረት መጥፋት አስከትሏል፡፡

## የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ እንዲሁም የተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎች መዘጋጀታቸውን በተመለከተ፤

39. የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የመቋቋሚያ አዋጅን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ደንቦችና መመሪዎች ሊያዘጋጅ እና በሚመለከተው አካል በማጸድቅ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ በተለይም መ/ቤቱ አገልግሎት ለሚሰጥባቸው ለቁፋሮ፣ ለላቦራቶሪ እና ለጂኦሳይንስ መረጃ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ ተመንን በተመለከተ የተዘጋጀና በሚመለከተው አካል የጸደቀና በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የክፍያ መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ጂኦሳይንስ መረጃ፣ ቁፋሮ (ድሪሊንግ) እና የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና ክብካቤ በተመለከተ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ የሌለ መሆኑ፣
- የላቦራቶሪ የአገልግሎት ክፍያ ተመን ዝርዝር በ2001 ዓ/ም የቁፋሮ እና የጂኦሳይንስ መረጃ የአገልግሎት ክፍያ ተመን ዝርዝሮች ደግሞ በ2003 ዓ/ም የተዘጋጁ ቢሆንም የክፍያ ተመኑ ከወቅቱ ዋጋ ጋር በማዛመድ ክለሳ ያልተደረገለት መሆኑን፣ የጂኦሳይንስ መረጃ እና የቁፋሮ (ድሪሊንግ) የአገልግሎት ክፍያ ተመን ዝርዝሮች በሚመለከተው አካል የፀደቁበት እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተፈቀደበት ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በተጨማሪም የጂኦሳይንስ መረጃ ክፍል ላይ የአገልግሎት ክፍያዎች የሚከናወኑት የክፍያ ተመን ዝርዝሩን መሰረት በማድረግ እንዳልሆነ እና በጽሁፍ ባልተቀመጠ ዋጋ መሆኑ፣

- መ/ቤቱ በ2000 ዓ.ም ባጠናው የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እና በላቦራቶሪ የዉስጥ መመሪያ ላይ በተገለፀው መሰረት ተገልጋዮች ናሙና ለማስመርመር ወደ ላቦራቶሪው በሚመጡበት ወቅት ናሙናዎቹን የላቦራቶሪው መስተንግዶ ክፍል ለባለሙያው እንዲደርስ ማድረግ የሚገባውና ተገልጋዩ የላቦራቶሪ ባለሙያውን በቀጥታ ማግኘት የማይገባው መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም ናሙና የሚያመጣው ተገልጋይ ምርመራውን ከሚያከናውነው ባለሙያ ጋር የሚገናኝ መሆኑ

ከተከለሱ መረጃዎች፣ መጠይቆችና የመስክ ምልከታዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. ስለሁኔታዉ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- በመ/ቤቱ የሚከናወኑ ስራዎች መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናትን (BPR)፣ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ የሚከናወኑ መሆናቸውን፣
- በ2003 ዓ.ም የተዘጋጀዉ የክፍያ መመሪያ ክለሳ ያልተደረገበት ምክንያት መ/ቤቱ የመንግስት ተቋም እንደመሆኑ መጠን ለትርፍ ተቋቋመ ባለመሆኑ እና እስካሁን በሰጠዉ አገልግሎት ወጪዉን በሚሸፍን መልኩ እያስከፈለ በመሆኑ እንዲሁም ቻርተር በማዘጋጀት በቻርተሩ በማስደገፍ እየተሰራ በመሆኑና በቀጣይ የወቅቱን ዋጋ ባገናዘበ መልኩ ለመከለስ የሚመለከተዉን አካል በማስፈቀድ የሚከለስ መሆኑን፣
- የጂኦሳይንስ መረጃ ዳይሬክቶሬት የሚጠቀምበትን የዋጋ ዝርዝር በተመለከተ በወቅቱ የተከለሰ ዋጋ ባለመፅደቁ በማኔጅመንት በተወሰነው መሰረት የሚሰራ መሆኑን፣ የጂኦሳይንስ መረጃ እና የቁፋሮ (ድሪሊንግ) አገልግሎት ክፍያ ዝርዝሮች አገልግሎት ላይ እንዲዉል በሚመለከተዉ አካል የፀደቀበት ደብዳቤ ያልተገኘ በመሆኑ ማቅረብ አለመቻሉን ነገር ግን የጂኦሳይንስ እና የድሪሊንግ መመሪያ በፍጥነት እንዲከለሱ በካውንስል ደረጃ ጠቀሜታ እንዳለው የታመነበት መሆኑን፣
- ደንበኛን ከማስተናገድ አንፅር ያሉ ክፍተቶች ማለትም ተገልጋዩ የናሙና ክፍል ባለሙያዎችን የሚያገኝበት ይህንን ጥቆማ መሰረት አድርገን በቀጣይ የማስተካከያ ስራ በመስራት መመሪያው በአግባቡ የሚተገበርበት ሁኔታ የሚመቻች መሆኑን

በቀረበላቸዉ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

42. በመ/ቤቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የተጠና ቢሆንም አዋጁን መሰረት ያደረገ መመሪያ ለየክፍሉ በተለይ ኦዲቱ ትኩረት ባደረገባቸው ክፍሎች ባለመዘጋጀቱና ለተዘጋጀለት ክፍልም መመሪያውን መሰረት አድርጎ የማይሰራበት ሁኔታ በመኖሩ መ/ቤቱ አገልግሎት ሰጪ ከመሆኑም አንፃር ስራዎች ወጥነት ባለው እና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን መልኩ እንዳይከናወኑ የሚያደርግበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ እንዲሁም የአሰራር መመሪያዎች አለመዘጋጀታቸውና የተዘጋጁትም በአግባቡ ሥራ ላይ አለመዋላቸው፣ ለቁፋሮ (ድሪሊንግ)፣ ለላቦራቶሪ እና ለጂኦሳይንስ መረጃ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢን በተመለከተ የተዘጋጀ የክፍያ ተመን ዝርዝር ከወቅቱ ዋጋ ጋር እንዲናበብ ሆኖ አለመከለሱ በዚህ ወቅት መ/ቤቱ መስጠት ያለበትን አገልግሎት በአግባቡ እንዳይሰጥ እና ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

## የመ/ቤቱን የናሙናዎች እና የንብረቶች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ፤

43. በመ/ቤቱ የሚገኙ የቁፋሮ /ድሪሊንግ፣ እና የላቦራቶሪ ንብረቶችን በአግባቡ ለመያዝና ለመጠቀም የሚያስችል የንብረት አያያዝና አጠቃቀምሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ያገለግሉ እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች (የቁፋሮ ማሽኖች፣ የላቦራቶሪ ማሽኖች፣ ኬሚካሎች) እና ለምርመራ የመጡ ናሙናዎች አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ

- ከተገልጋዮች የሚመጡ ናሙናዎች በተዝረከረከ ሁኔታ የሚቀመጡ መሆኑን፣
- ምርመራቸው የተጠናቀቀ ናሙናዎች በመ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ ከ30 ዓመት በላይ በላይ ተጠራቅመው የተቀመጡ መሆኑን፣



*ምስል 1፡- በላቦራቶሪው መጋዘን የተቀመጡና መወገድ የሚገባቸው ናሙናዎች*

- መካኒሳ በሚገኘው የላቦራቶሪው መጋዘን ውስጥ በባህርይ የማይገናኙ ንብረቶች እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆናቸውን፣ በመካኒሳና በዋናዉ ግቢ ዉስጥ የሚገኙ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የቁፋሮ (ድሪሊንግ) መሳሪያዎች እንዲሁም ጥገና ቢደረግላቸው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የማዕድን ቁፋሮ ማሽኖች (ሪጎች) ሜዳ ላይ በመቀመጥ ለፀሀይና ለዝናብ በመጋለጥ አግባብ ላልሆነ ብክነት የተዳረጉበት ሁኔታ መኖሩን፣ በተጨማሪም በ1979 ከጃፓን (የዋጋ መጠናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው) ተገዝተው የገቡ ማሽኖች እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆናቸውን፣



ምስል 2፡- *በመካኒሳ ግቢ ውስጥ ያለመጠለያ የተቀመጡ ሪጎች በከፊል*

- ICP-OES (Inductively Coupled Plasma Optical Emission Spectrometry) የተባለው ማሽን ከ7 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑን፣

- በወቅቱ AAS (Atomic Absorbtion Spectrometer) የተባለው ማሽን በቁጥር ሁለት የተገዛና አንዱ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ሁለተኛው ያለአገልግሎት ከ5 አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑን፣
- የላቦራቶሪው ዕቃ ግምጃ ቤት ከ2007-2009 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ውስጥ ቆጠራ ተደርጎለት የማያዉቅና የቋሚ ዕቃ መዝገብ የሌለው መሆኑን፣
- በመ/ቤቱ ዋናው ግቢ እና መካኒሳ በሚገኙ መጋዘኖች ዉስጥ ያገለግሉ በርካታ የቁፋሮ/የድሪሊንግ/ ማሽኖች (ጀነሬተር፣ መቆፈሪያዎች፣ ሪግ)፣ የላቦራቶሪ ማሽኖች (ወንፊቶች፣ የድንጋይ መቁረጫ ምላጮች፣ የድንጋይ መቁረጫ መሳሪያ፣ የድንጋይ ማሻ ዲስክ፣ የድንጋይ ማሻና ማለስለሻ መሳሪያ፣ ማይክሮስኮፖች፣ ትራንስፎርመር እና አልትራ ቫዮሌት ላምፕ) ለረጅም አመታት የተቀመጡ መሆኑ እንዲሁም በሻሸመኔ እና በአዲስ አበባ ባሉ የመ/ቤቱ ዕቃ ግምጃ ቤት አገልግሎት ያለፈባቸዉ የተከማቹ የድሪሊንግ እና የላቦራቶሪ (ጠጣርና ፈሳሽ) ኬሚካሎች መኖራቸውን፣

በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡





*ምስል 3፡- የማያገለግሉና ሳይወገዱ የተቀመጡ የላቦራቶሪና ድሪሊንግ ዕቃዎች ለማሳያ*



*ምስል 4፡- ለረጅም ጊዜ ሳይወገዱ የተቀመጡ ኬሚክሎች በከፊል /መካኒሳ መጋዘን/*

45. ስለሁኔታዉ የመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች

- ናሙናን ለመያዝና ለማስወገድ የሚያስችል መመሪያ ያልነበረ ሲሆን አዲስ እየተዘጋጀ ባለዉ ISO -17025 Quality ማንዋል ዉስጥ የተካተተ መሆኑን፣ በላቦራቶሪዉ መጋዘን ዉስጥ ለረዥም አመታት የተቀመጡ ናሙናዎችን ለማስወገድ ጨረር አምጪ ያለመሆናቸዉን በሚመለከተዉ አካል ከተረጋገጠ በኋላ ለማስወገድ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣
- የቁፋሮ /ድሪሊንግ ዕቃዎችን በተመለከተ የሚያገለግሉ የሌሉ ቢሆንም ዕቃዎች በአግባቡ መቀመጥ የሚገባቸዉ መሆኑን፣ በዋናው ግቢ የሚገኘው ቬንትሌተር የመጣዉ ለቁፋሮ (ድሪሊንግ) አገልግሎት ባለመሆኑ የማያገለግል መሆኑን በማረጋገጥ የማስወገድ ስራ የሚሰራ መሆኑን፣
- የቁፋሮ/ድሪሊንግ ዕቃዎች እና የወርክ ሾፕ ዕቃዎችን በተመለከተ የሚሰሩትንና የማይሰሩትን ለመለየት ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሰራ ሲሆን ስራዉን እንደጨረሰ የማይሰሩት በመመሪያዉ መሰረት የሚወገዱ መሆኑን እና በሌሎች መጋዘኖች ያሉትንም በተመሳሳይ መልኩ አዲስና አሮጌ ተለይቶ ዳግመኛ አገለግሎት የማይሰጡት በመመሪያዉ መሰረት የሚወገዱ መሆኑን፣
- አገልግሎታቸዉ ያለቁ ኬሚካሎችን ለማስወገድ በአገር አቀፍ የተቋቋመ ተቋም ባለመኖሩ በሰርቬዩ አቅም ማስወገድ የማይቻል ሲሆን ጉዳዩ ሃገራዊ ትርጉም የተሰጠዉ በመሆኑ ሰርቬዩ ፎካል ፐርሰን መድቦ ክትትል እያደረገ መሆኑን፣

- Inductively Coupled Plasma - Optical Emission Spectrometry (ICP-OES) እና Atomic Absorbation Spectrometre (AAS) የተባሉ መሳሪያዎች በሰው ሃይልና ግብአት እጥረት ከተገዙ በኋላ ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጡ ከ6 አመት በላይ ያስቆጠሩ መሆናቸዉን፣ ግዥ ሲፈፀም የአዋጭነት ጥናት ያልተደረገ መሆኑን እንዲሁም በመሳሪያዎች ግዥ ወቅት የነበሩ ማስረጃዎች በላቦራቶሪው ውስጥ ያልተገኙ መሆናቸዉን እና በቀጣይ መሳሪያዉን ለሚጠቀም መንግስታዊ ተቋም ሰርቬዩ ጠግኖ እንዲያስረክብ ዉል የመፈራረም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን፣
- በቦታ እጥረት ምክንያት በባህሪይ የማይገናኙ ዕቃዎች በጋራ የሚገኙ መሆናቸዉንና በቀጣይ የሚስተካከል መሆኑን፣
- ቆጠራን በተመለከተ በላቦራቶሪ ዕቃ ግምጃ ቤት የተጠቀሰዉ ትክክል ቢሆንም በ2009 ዓ/ም ቆጠራ ተጀምሮ አሁን እየተጠናቀቀ መሆኑን እና በላቦራቶሪ ዕቃ ግምጃ ቤት ቋሚ ንብረቶችን ለመመዝገብ የሚያስችል የቋሚ ዕቃ መዝገብ የሌለና ይህን ለማሟላት እየተሰራ መሆኑን፣

በቀረበላቸው መጠይቅ፣ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

46. የመ/ቤቱ ንብረቶች፣ ኬሚካሎች እና ናሙናዎችን ለመያዝና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የሚያገለግሉ ንብረቶች አለአግባብ ተቀምጠው ማስገኘት ያለባቸውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሳያስገኙ እንዲቀሩና አገልግሎት የመስጠት አቅማቸውን እንዲያጡ የሚያደርግ ሲሆን፣ የማያገለግሉ ንብረቶች ደግሞ ሳይወገዱ በመቀመጣቸው አግባብ ያልሆነ ወጪ እንዲያስወጡ አድርጓል፡፡

### የኮርና የአለት ናሙናዎች አያያዝ እና አመታዊ ቆጠራ መደረጉን በተመለከተ፤

47. በየጊዜው የሚሰበሰበውን የኮርና የአለት ናሙና በተገቢው መልኩ መያዝና በዳታ ቤዝ በማስገባት በአመት ሁለት ጊዜ ቆጠራ ሊደረግ ይገባል፡፡

48. በየጊዜው የሚሰበሰበውን የኮርና የአለት ናሙናዎች በዳታ ቤዝ በማስገባት በአመት ሁለት ጊዜ ቆጠራ መደረግ እንዳለበት መ/ቤቱ ባጠናው የመሰረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፡-

- ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ በመ/ቤቱ የተሰበሰቡ ኮርና የአለት ናሙናዎች ቆጠራ ሪፖርት ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑን እንዲሁም ናሙናዎቹ የሚቀመጡበት እንደሙዚየም ያገለግላል የተባለው መጋዘን ንፅህናው የተጠበቀ ካለመሆኑ የተነሳ የናሙና መደርደሪያውን ምስጥ እየበላው ያለበት ሁኔታ መኖሩን፣
- የኮር እና የአለት ናሙናዎች ደህንነታቸው ባልተጠበቀ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸው እንዲሁም የአለት ናሙናዎች በተቀዳደዱ ማዳበሪያዎች መሬት ላይ ተበታትነው የሚገኙ እና መደርደሪያ /ሼልፍ/ ላይ የተቀመጡትም በተገቢው መልኩ ምንነታቸውን የሚያሳይ መግለጫ ያልተቀመጠ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠይቅ፣ በተከለሱ ዶክመንቶችና በአካል በመመልከት ለመረዳት ተችሏል፡፡



*ምስል5፡- በአግባቡ ያልተቀመጡ የኮር እና የአለት ናሙናዎች*

49. ስለጉዳዩ የጂኦሳይንስ መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት ምላሽ የኮርና የአለት ናሙናዎች ላይ አመታዊ ቆጠራ አለመደረጉን፣ የኮርና የአለት ናሙናዎች አቀማመጥ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ እንዳልሆነና አሁን ባለበት ሁኔታ ሙዚየም ነው ለማለት የማያስችል እና የሙዚየም መልክ እንደሌለው በሰጡት ምላሽ አስረድተዋል፡፡

50. ስለሁኔታዉ የመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች የኦዲት ግኝቱ ትክክል መሆኑንና ይህንን ችግሩን ለመቅረፍ ባለሁለት ፎቅ ሙዚየም ለመስራት ታስቦ ለገንዘብ ሚኒስቴር በ2005 ዓ.ም ጥያቄ ቀርቦ እንደነበረና ቦታዉ ላይ የሚፈቀደዉ ባለሰባት ፎቅ እና ከዚያ በላይ በመሆኑ ለፕሮጀክቱ የተፈቀደው 1 ሚሊዮን ብር ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ባለሰባት ፎቅ እና ከዚያ በላይ ለመገንባት ጥያቄ ቀርቦ የነበረና ለዚህ ስራ ቅድሚያ እንደማይሰጥ ስለተገለፀ ስራዉ በዚህ ሁኔታ የተቋረጠ መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

51. በየጊዜው የሚሰበሰቡ የኮርና የአለት ናሙናዎች ሥርዓት ባለው መልኩ አለመቀመጣቸውና አለመጠበቃቸው እንዲሁም የተደራጀና ደረጃውን የጠበቀ የኮርና የአለት ናሙናዎች ማሳያ ሥፍራ /ሙዝየም ባለመኖሩ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን አገልግሎት በቀላሉ ማግኘት እንዳይችሉ እንዲሁም ወጪ ወጥቶባቸው የተሰበሰቡ የሀገሪቱን የማዕድን አቅም ሊያሳዩ የሚችሉ ናሙናዎች እንዳይታወቁ ያደርጋል፡፡

## የመስሪያ ቤቱን ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም በተመለከተ፤

52. የተለያዩ የማዕድን ፍለጋ ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም መርሀ ግብር ሊዘጋጅላቸውና በመርሀ ግብሩ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የመ/ቤቱን የሶስት አመታት ማለትም ከ2007-2009 ዓ/ም ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማየት እና ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- የሰው ሀይል ፍልሰት በከፍተኛ ሁኔታ ያለበት መስሪያ ቤት እንደሆነ በተደጋጋሚ በችግር እየተገለጸ ዕቅዶች ከፍተኛ (ከ100%- እስከ 500% በላይ) አፈፃፀም ማሳየታቸው መ/ቤቱ ዕቅድ ሲያቅድ ጥናትን መሰረት የማያደርግ መሆኑን፣
- በየአመቱ ዕቅድ ሲታቀድ የመጀመሪያውን አመት አፈፃፀም በማየት ለቀጣዩ አመት ማሻሻያ ማድረግ የሚገባ ሲሆን በዚህ መልኩ የማይታቀድና ከአቅም በታች በማቀድ ከፍተኛ አፈፃፀም እንዲታይ የሚደረግ መሆኑን፣
- በሌላ በኩል በመ/ቤቱ ዝቅተኛ አፈፃፀም የሚታይባቸው ዕቅዶች መኖራቸውን ለምሳሌ የላቦራቶሪ አገልግሎቶችን ለመስጠትና ለማከናወን የታቀዱ ዕቅዶች ከመቶዉ 12 እስከ 45 መሆኑን፣ የሜታሊክስ ማዕድናት (የደለል ወርቅ) ፍለጋና ጥናትን አፈጻጸም ከ27-42 ከመቶ መሆኑን፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ማዕድን ፍለጋና ልማት ፕሮጀክትን ከ3-43 ከመቶ መሆኑን፣ የመስክ ሪፖርትና ካርታ ዝግጅት 20 ከመቶ እና ቁፋሮ (ድሪሊንግ) ከ3-47 ከመቶ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ከላይ የተገለፁትን ክፍተቶች ዝርዝር በአባሪ 3 እና 4 ይመልከቱ)

54. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- አፈፃፀማቸው ከ2007-2009 ዓ/ም ያለው መ/ቤቱ የተቋቋመበትን አላማ ከማሳካት አንፃር በዋናነት በሰው ሀይል ፍልሰትና በተሽከርካሪ ችግር የተነሳ አፈፃፀሙ በአብዛኛው በሚባል ደረጃ ከዕቅድ በታች ቢሆንም በአንድ ፕሮጀክት ወይም ዋና ተግባር በመስክ ስራ ወቅት በሚያጋጥም የጂኦሎጂ አፈጣጠር ምቹ መሆን አለመሆን እንዲሁም በውጭ እርዳታ ከዕቅድ በላይ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በድምሩ ሲታይ በአብዛኛው ከዕቅድ በታች መሆኑ፣ የተወሰኑ ስራዎች ከዕቅድ በላይ መከናወን ከተፈጥራዊ ሁኔታዎች እና ከውጭ በተገኘ ድጋፍ የተከናወነ እንጂ ሆን ተብሎ ከአቅም በታች በማቀድ ከፍተኛ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ታስቦ ባለመሆኑ፣
- ከ2007-2009 ዓ.ም የድሪሊንግ አፈፃፀም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ማሽኖች ከ30 አመት በፊት የተገዙና ያገለገሉ በመሆናቸዉ፣ መለዋወጫ በወቅቱ ባለመገዛቱ፣ የጥገና መዘግየት በመኖሩ፣ በኦኮቴ የሪግ መቃጠል አደጋ በመድረሱ፣ የሰርቪስ መኪና ችግር በመኖሩ፣ የመ/ቤቱ የውስጥ የቁፋሮ ስራ ሙሉ በሙሉ በመቆሙና ከዉጭ የሚመጡ ጥያቄዎች በቂ ባለመሆናቸዉ፣ የድሪሊንግ ስራ ለማሰራት ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ ስለሆነ የቁፋሮ ስራ መስራት የማይችሉ በመሆኑ የማዕድን ክለላ ተደርጎ መረጃው ለኢቨስተሮች እንደሚቀርብና ዝርዝር የሆነው የማዕድን ፍለጋ እና የክምችት መጠንን የማወቅ ስራ ለኢንቨስተር የሚተው ስራ በመሆኑ፣
- የላቦራቶሪ አገልግሎቶችን ለመስጠትና ለማከናወን የታቀዱ ዕቅዶች ከመቶዉ 12% እስከ 45% የሆነበት ምክንያት የሰው ሃይል፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ በመኖሩ፣ ጥቁር ገበያ በመጨመሩ ምክንያት የወርቅ ባር አቅርቦት የቀነሰ በመሆኑ፣
- የሜታሊክስ ማዕድናት (የደለል ወርቅ) ፍለጋና ጥናት አፈፃፀም ከ27-42 በመቶ መሆኑን በተመለከተ ቀደም ሲል በ2008 ዓ/ም የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሲዘጋጅ በየአመቱ ለማካለል የታቀዱትን የአለኝታ ቦታዎች ለማሳካት የተሽከርካሪዎች ፍላጎት በማሟላት የመስክ ቡድኖችን ቁጥር

በመጨመር የታቀደ ቢሆንም ይህ ባለመሆኑ በመርሀ ግብሩ የተመለከተውን ግብ ማሳካት ባለመቻሉ፣

- በምዕራብ ኢትዮጵያ ማዕድን ፍለጋና ልማት ፕሮጀክት ላይ የሚሰራው የቻይና ኩባንያ ስራዉን በማቋረጡ፣ በ2008 ዓ.ም ወደ መስክ ለመሰማራት የፀጥታ ችግር በመኖሩ፣ በደለል ወርቅ ዙሪያ የባለሙያ ፍልሰትና የመስክ ተሽከርካሪ እጥረት በመኖሩ፣ የተሰሩ ስራዎች በነበረን የማስፈፀምና የተቋማችን የባለሙያ አቅም መጠን የተሰሩ በመሆኑ፣
- የማጠቃለያ ሪፖርትን በተመለከተ በመስክ መረጃ ላይ በመመስረት የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን በላቦራቶሪ የተላኩ ናሙናዎች በርካታ በመሆናቸዉና በአቅም ውስንነት ምርመራው ረዥም ጊዜ የሚጠይቅ ስለሆነ ሪፖርቱ እንደደረሰ የሚጠናቀቅ በመሆኑ፣
- በመ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ የተከሰተው የሰው ሀይል ፍልሰት ያመጣው ችግር መሆኑን እንዲሁም ቁፋሮን (ድሪሊንግ) በተመለከተ GTPውን ለማሳካት ሲባል ብቻ ስራው ባይኖርም የሚታቀድ በመሆኑ፣

ምክንያት አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ሊሆን እንደቻለ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

55. ከዕቅድ በላይ የተሰሩትን በተመለከተ ደግሞ

- በተለይ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች፣ በመልካም አስተዳደር፣ በኤ.ች.አይ.ቪ. እና በሴቶች ዙሪያ ከዕቅድ ዉጭ የሚሰጥበት ሁኔታ በመኖሩ፣ በዉጭ ሀገር የሚሰጡ ስልጠናዎች እንደ አመጣጣቸው የሚሰጡ በመሆኑ እና በትክክል ማቀድ አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- የስነ ምድር ሁኔታ (Geological setting) አስገዳጅና አበረታች በሚሆንበት ጊዜ ከዕቅዱ በላይ ናሙና ስለሚሰበሰብ እና የፒት ቁፋሮ የሚደረግ በመሆኑ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍለጋ በፊንላንድ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሚደገፍ በመሆኑ

አፈፃጸማቸው ከፍ ሊል እንዳቻለ በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

- በአጠቃላይ ከዕቅድ ውጭ የሚሰሩ ስራዎችን ከዕቅዱ ውጭ ስለመሰራታቸው በመግለፅ ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ግንዛቤ የተወሰደ በመሆኑ በቀጣይ በዚህ መልኩ የሚሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

56. ኃላፊዎች ከላይ የተጠቀሰውን ምላሽ ቢሰጡም

- ዕቅድ ሲታቀድ መልካም አጋጣሚዎችን፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን፣ ለችግሮች የሚሰጡ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እንዲሁም መ/ቤቱ ያለውንና ሊኖር የሚችለውን ግብዓት (Resourse) ከግምት ውስጥ በማስገባት መታቀድ ያለበት በመሆኑ፣ እንዲሁም የውስጥ ቁፋሮ (ድሪሊንግ) ስራ እንዲቆም መሰረት ሆነ የተባለው ጥናት እንዲሁም ማንኛውም የአሰራር ለውጥ መደረጉን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበና ይህ ጥናት ወይም የአሰራር ለውጥ አለ እየተባለ ባለበት ሁኔታ በውስጥ የቁፋሮ ስራ እንዲሰራ እየታቀደ የሚገኝ በመሆኑ ከፍተኛ ለሆነው የእቅድ አፈፃፀምም ሆነ ለዝቅተኛ ዕቅድ አፈፃፀም የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

57. መ/ቤቱ በተዘጋጀው የስትራቴጂክ ሆነ ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ስራውን ባለመከናወኑ እና ዕቅዱ ከአመት አመት ያመጣው አፈፃፀም እየታየ በዛው ልክ ዕቅዱ እንዲስተካከል ማድረግ ባለመቻሉ መስሪያ ቤቱ ባለው አቅም ምን መስራት እንዳለበትና ምን እንደሰራ ማረጋገጥን አዳጋች በማድረግ በማዕድን ፍለጋ አስመልክቶ የሚቀርበውንም ሪፖርት ተአማኒነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

## 2.2. መረጃ አያያዝ፣ አሰጣጥና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር መገምገም፣

**በማዕድን ስራ ከተሰማሩ ተቋማት የጂኦሳይንስ መረጃዎችን መሰብሰብን፣ በዘመናዊ መልኩ ማደራጀትን፣ ማሰራጨትና የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤**

58. መ/ቤቱ የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዋወቅ እና በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

59. ይሁን እንጂ

- የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዋወቅ እና በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት የሚያስችል መመሪያ የሌለ መሆኑን፣

- ከማዕድን እና ተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ ከውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚ/ር፣ ከክልል ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮዎች እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተጠኑ የማዕድን ጥናቶች መረጃ ወደ መ/ቤቱ ወጥ በሆነ መልኩ የማይሰበሰቡ መሆኑን፣
- በመ/ቤቱ የተሰበሰቡ ናሙናዎች አስፈላጊውን መረጃ አካተው ለተገልጋይ ዝግጁ ለማድረግ ቢታቀድም በእቅዱ መሰረት የማይከናወን መሆኑን፣
- የተሰበሰቡ መረጃዎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም ዌብ ሳይትና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የማይተዋወቁ መሆኑን፣
- የኮርና የአለት ናሙናዎችን ደህንነት ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ ደረጃዉን የጠበቀ ጂኦሙዚየሙ በማደራጀትና የተለያዩ ጎብኝዎችን በመጋበዝ፣ በቴምብር ላይ ምርጥ ናሙናዎች እንዲወጡ በማድረግ፣ ፖስተር በማዘጋጀትና በማሰራጨት፣ በራሪ ወረቀት በማደል እና አውደ ርዕይ በማዘጋጀት የማዕድን ዘርፉን የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራቱን፣
- በጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ ላይ የዳታ ቤዝ ባለሙያም ሆነ የሚሰራ የዳታ ቤዝ ስራ አለመኖሩን

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. ስለሁኔታው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ

   - የጂኦሳይንስ ስራዎችን ሰብስቦ ለማደራጀት፣ ለተገልጋዮች ለማስተዋወቅ እና ለማሰራጨት የሚያስችል ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እና ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር የሚያደርግ መመሪያ አለመኖሩ የሚለው ትክክል መሆኑ እና አሁን እየሰራ ያለው በፒአር ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆኑንና የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ እየተዘጋጀ መሆኑን፣
   - የጂኦሳይንስ መረጃ በግልፅና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለመስራት በአሁኑ ወቅት በሚሻሻለው አዋጅ ላይ ደንብና መመሪያ እንዲኖረው ታስቦ እየተሰራ መሆኑን፣
   - ከተለያዩ ተቋማት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን በየዓመተ ምህረቱ፣ ከየት መ/ቤት እንደመጣ እና ሌሎች መካተት የሚገባቸው ጉዳዮች ባለመኖራቸው ይህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲስተካከል ስራዎች እንዲሰሩ አቅጣጫ የተሰጠ መሆኑን፣

- ሰርቬዩ ዕቅድ ይዞ እየሰራ ቢሆንም መተዋወቅ ያለበትን ያህል እያስተዋወቀ አለመሆኑና በአሁኑ ሰዓት ጥልቅ መረጃዎች እየተለቀቁ እንደሆነና በቀጣይ ፖሊሲው ሲፀድቅ ችግሩ ተፈትቶ በሰፊው የማስተዋወቅ ስራ የሚሰራ መሆኑን፣
- በጂአሳይንስ ላቦራቶሪ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም ይህንን ስርዓት ተጠቅሞ ስራዎችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመስራት ባለሙያ ከገበያው ባለመገኘቱ መሆኑን፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

61. መ/ቤቱ የስነ ምድር መረጃዎችን ከተቋማት በመሰብሰብ ለተገልጋይ ዝግጁ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ ተጠቃሚዎች ጥራቱን የጠበቀና ወቅታዊ የሆነ መረጃ በተሟላ መልኩ እንዳያገኙ እና የማዕድን ኢንቨስትመንት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## የተገልጋዮች የአገልግሎት አሰጣጥና መረጃ እርካታ ደሰሳ ጥናትና ቅሬታ አፈታትን በተመለከተ፤

62. መ/ቤቱ የተገልጋዮችን /የባለድርሻዎችን እርካታ የሚያሳይ የደሰሳ ጥናት ሊያከናውን እና የተገልጋዮች ቅሬታ አፈታት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
63. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የባለድርሻዎችን እርካታ የሚያሳይ የደሰሳ ጥናት የተከናወነ መሆኑን በሶስቱ አመታት (2007፣ 2008 እና 2009 በጀት አመታት) ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ቢገለጽም ተከናወነ የተባለው የደሰሳ ጥናት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃው አልቀረበም፡፡
64. ቅሬታን በተመለከተ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከጽ/ቤቱ ካሉ ሰራተኞች ተቋቁሞ እየሰራ ቢገኝም የዉጭ ተገልጋይ ቅሬታን ያካተተ ማስረጃ ለማየት ያልተቻለና የዉጭ ተገልጋይ ቅሬታ መጥቶ የተፈታበት ሁኔታ መኖሩን ለማየት የሚያስችል ማስረጃ ባለመቅረቡ የተገልጋዮች ቅሬታና አቤቱታ አፈታት ስርዓት በተሟላ መልኩ እንዳማይከናወን ለመረዳት ችለናል፡፡
65. ስለጉዳዩ ለጂአሳይንስ መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በክፍሉ የእርካታ ደሰሳ ጥናት ለማድረግ ታስቦ ለተገልጋዮች ቃለ መጠይቅ በማዘጋጀት መረጃ ቢሰበሰብም የተጠቃለለ የዳሰሳ ጥናት አለመከናወኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

66. ስለሁኔታው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በየስራ ክፍሉ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት አስተያየት የሚሰጡበት መዝገብ እንዳለ ነገር ግን ይህንን በማደራጀት አጥንቶ የተገልጋዮችንና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ለይቶ ስራ ላይ የማዋል ችግር መቀረፍ ያለበት መሆኑን፣ ለውጭ ተገልጋይ ብቻ የሚያገለግል የሀሳብ መስጫ ሳጥን በተለይ ለላቦራቶሪ፣ ለድሪሊንግ እና ለጂኦሳይንስ መረጃ መቀመጥ እና በየጊዜው መገምገም እንዳለበት የሚያምኑ መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ አስረድተዋል፡፡

67. መ/ቤቱ የተገልጋዮች /ባለድርሻዎች እርካታ የሚያሳይ ደሰሳ ጥናት ባለማከናወኑ ያሉበትን ክፍተቶች መለየትና የተገልጋዮች እርካታ ያለበትን ደረጃ ለማየት የሚያስቸግር ሲሆን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ስርዓት ተዘርግቶ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ባለመሆኑ ተገልጋዮች ቅሬታቸዉን በአግባቡ እንዳያቀርቡና በአገልግሎት አሰጣጥ የሚያጋጥመውን ችግር መፍታት እና አሰራሮችን ማስተካከል እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የስልጠና አሰጣጥ ግምገማ ሥርዓትን በተመለከተ፤

68. መ/ቤቱ በማዕድን ፍለጋ፣ በላቦራቶሪ፣ በቁፋሮ (ድሪሊንግ) እና ጂኦሳይንስ መረጃ ላይ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በዕቅድ የተደገፈ ስልጠና ሊሰጥ እና የሚሰጡ ሥልጠናዎች የሚገመገሙበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ፡-

- የስልጠናውን አስፈላጊነትና ለሚመለከተዉ አካል ስልጠናዉ መሰጠቱ የሚለይበት ፖለሲና የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ ስልጠናዎች በእኩልነት ለሚመለከተው ባለሙያ የማይሰጥ መሆኑን እንዲሁም በላቦራቶሪው የሚሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት የተገመገመ አለመሆኑ በመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ላይ መገለጹን፣
- ለሰራተኛው ስለ መሳሪያዎች አጠቃቀም በቂ ሥልጠና ባለመኖሩ መሳሪያዎቹን በአግባቡ መጠቀም ያልተቻለ እና ችግሩም እስካሁን ያልተቀረፈ መሆኑን የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስናና ጥገና እንክብካቤ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እና በሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ላይ ለማወቅ መቻሉን፣

➢ በቂ የሆነ የስልጠና ጊዜ ተገድቦ ባለመቀመጡ አስፈላጊው ስልጠና የማይሰጥበት ሁኔታ መኖሩን፣ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች እንዲሳተፉ አለመደረጉ፣ ኬሚስቱ እንደ ጂኦሎጂስቶች የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ስልጠና የማያገኝበት ሁኔታ መኖሩን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና ከቀረቡ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

70. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች

➢ በውስጥ የኦዲት ሪፖርት ላይ በላቦራቶሪ የሚሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ዉጤት ያልተገመገመበት ምክንያት ቀደም ብለው የሰለጠኑ ባለሙያዎች 90% በላይ የለቀቁ በመሆናቸው መሆኑን፣

➢ የሃገር ውስጥ ስልጠናዎች ከመንግስት በሚመደብ በጀትና ክፍሎች በሚያቅዱት የስልጠና ፍላጎት መሰረት መሆኑንና ስልጠናው አስፈላጊ መሆኑን አጣርቶ የሚልከው የቅርብ አለቃ መሆኑን የስልጠና ክፍሎችም ይህንኑ እንደሚያረጋግጡ፤ የውጭ ስልጠናን በተመለከተ ግን ስልጠና የሚሰጠው አካል በሚጠይቀው ሙያና መስፈርት መሰረት በመሆኑ በመስፈርቱ መሰረት ተወዳድረው ላለፉ እድሉ የሚሰጥ ስለሆነና በእኩል ደረጃ የሚሰጥ ላይሆን የሚችል መሆኑን

➢ ለአንዱ ባለሙያ የመጣ የስልጠና ዕድል ለሌላ የሚሰጥበት ሁኔታ እንደሌለና ለሚመለከተው አካል (ባለሙያ) እንዲሰጥ የሚደረግ መሆኑን

በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

71. ሥልጠናዎች በፖሊሲ፣ በሥርዓትና በዕቅድ አለመመራታቸው፣ ተገቢው ስልጠና ለተገቢው ባለሙያ አለመሰጠቱ እና ያመጣው ውጤት አለመገምገሙ መ/ቤቱ የተቋቋመበትን አላማ እንዳያሳካ እና የአቅም ግንባታ ሥራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## በሥራ ላይ የሰራተኞች ደህንነት አጠባበቅን በተመለከተ

72. በስራ ላይ የሰራተኞች (በተለይ የሴቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያደርጋቸው መልኩ) ደህንነትና ጤና ሊጠበቅ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡

73. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ከ2007-2009 ዓ/ም በቁፋሮ (Drilling)፣ በማዕድን ፍለጋ እና በላቦራቶሪ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ዕቅድ አለመኖሩን፣
- የጂኦኬሚካል ላቦራቶሪ እና የሚኒራሎጂና ጂኦቴክኒካል ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በላቦራቶሪው ውስጥ ለምርመራ የመጡና ምርመራ የተጠናቀቀላቸዉ ናሙናዎች እና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸዉ (expired) ኬሚካሎች በአካባቢ እና በሰራተኞች ላይ ስለሚያደርሱት ጉዳት ጥናት ባልተጠናበት እና ጥንቃቄ ባልተደረገበት ሁኔታ በመጋዘን ዉስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን፣
- የደህንነት መሳሪያዎች ላይ እስካሁን ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑን፣
- ለሰራተኞች አገልግሎት የሚውል ጥራት ያለዉ ጋዋን፣ የአይን መነፀር (google)፣ ጓንት፣ ፎጣ፣ የአቧራ መከላከያ፣ ጓንት እና ቆብ (ሄልሜት) በተሟላ መልኩ የሚቀርብ አለመሆኑንና የሚገዙትም ጥራት የሚጎላቸው መሆኑን፣
- የኬሚካል ትነት ወደ ውጭ ለማስወጣት የሚችለው ሁድ (extractor) በመጎዳቱ የኬሚካሉ ትነት በላቦራቶሪ ውስጥ ያለዉን አየር የሚበክልና ከሰራተኛ አልፎ በአካባቢው ነዋሪ ጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ትኩረት ባለማግኘቱ ሰራተኞች ደህንታቸዉ ባልተጠበቀበት ሁኔታ እየሰሩ መሆኑን፣
- ሴት ሰራተኞች ከወንዶች በተለየ መልኩ ደህንነታቸዉን ለመጠበቅ የሚታቀድ ዕቅድ እና የሚሰራ ስራ አለመኖሩን

ለማወቅ ችለናል፡፡

74. ስለሁኔታዉ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- የደህንነት መሳሪያዎች ላይ እስካሁን ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ ቢሆንም በ2010 ዓ/ም ስልጠና ለመስጠት ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ ማንኛውም የሙያ ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት በስልጠናው ማጠቃለያ ደህንነትን በተመለከተ ገለፃ የሚደረግ ቢሆንም ራሱን በቻለ ሁኔታ ዕቅድ ተይዞለትና ወጥ በሆነ መልኩ ደህንነትን

በሚመለከት ለሰራተኞች ስልጠና የማይሰጥ መሆኑን፣ በመመሪያው መሰረት በላቦራቶሪ ላሉ ሰራቶኞች ደህንነት መጠበቂያ ወተትና የስራ ላይ መገልገያ የሚሰጥ መሆኑን፣ ሰርቬዩ የጤና ደህንነት ባለሙያ መድቦ መረጃዎች እየሰባሰበና አቅም በፈቀደ መጠን ግብዓቶችን ለመሟላት በጀት እየተመቻቸ መሆኑን እንዲሁም ካለፈው በጀት ዓመት ጀምሮ ለፐብሊክ ሰርቪስና ለሰው ሀብት ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር የተጀመረ መሆኑን፣

- ሴቶችን በተመለከተ ግኝቱ ትክክል እንደሆነና ሴቶችን በተለየ መልኩ የሚጠብቅ አሰራር ባይኖርም እንደማንኛውም ሰራተኛ የሚቀርቡ የደህንነት መጠበቂያ አገልግሎቶችን እንደስራቸው ባህሪያት የሚያገኙ መሆኑን (በተለይ የላቦራቶሪ ሰራተኞች)፣ የደህንነት ዕቃዎች ጥራትን በተመለከተ በተለይ ጓንት የመሳሰሉት መገልገያዎች ጥራት የሌላቸው በመሆኑ አስቸጋሪ መሆናቸውን፣
- ኬሚካሎች ተለይተው በመጋዘን ውስጥ የተቀመጡ ሲሆን በሰርቬዩ አቅም የማይወገዱ በመሆናቸውና በሃገር አቀፍ ደረጃ ኬሚካልን የሚያስወግድ ተቋም ስለሌለ ችግሩ እስካሁን ያልተቀረፈ መሆኑን፣ የኬሚካል ትነትን ወደ ውጭ ለማስወጣት የሚችለውን ሁድ በተመለከተ ሶስት ሁዶች በአሁኑ ሰዓት የተጠገኑ ቢሆንም ሌሎችም ከሰባት በላይ የሚደርሱ ሁዶች አቅማቸው ጭምር የደከመ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ችግሩ መኖሩ እና በቀጣይ ከባብያዊ እና ሰራተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የስራ ቦታ ለመፍጠር ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ አስረድተዋል፡፡

75. መ/ቤቱ በማዕድን ፍለጋ፣ በድሪሊንግ እና በላቦራቶሪ የሚሰሩ ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ምቹ የስራ አካባቢ አለመኖሩ፣ ጥራት ያላቸዉ የሴፍቲ እቃዎች በተሟላ መልኩ አለማቅረቡና የሰራተኞቹን ደህንነት አለመጠበቁ በሰራተኞች በተለይም ሴት ሰራተኞች ላይ በጤናቸው ላይ ጉዳት ከማስከተሉም ባሻገር የሥራ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

76. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑ በሚገመገምበት ወቅት የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- በእያንዳንዱ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ላይ በየደረጃው በሚመለከተው አካል/ባለሙያ ጥራቱ እንዲረጋገጥ የማይደረግ መሆኑ፣
- ላቦራቶሪው ላይ በገለልተኛ አካል ግምገማ የማይደረግ መሆኑ፣
- የላቦራቶሪው የጥራት ማረጋገጫ የማግኘት ሂደት ከ10 ዓመት በላይ ተግባራዊ አለመሆኑ በዚህም ምክንያት ወደ ውጭ ለምርመራ የሚላክ የናሙና መጠን እየጨመረ መምጣቱ፣
- መ/ቤቱ ሥራ ለሚሰራባቸው መሳሪያዎች መደበኛ ጥገና የማይደረግላቸውና ካሊብሬት መደረግ ያለባቸውም የማይደረጉ መሆኑ፣
- መ/ቤቱ የቁፋሮ (ድሪሊንግ) አገልግሎት ለመስጠት ውል ከተዋዋለ በኋላ በገባው ውል መሰረት የማይፈጽም መሆኑ፣
- በመ/ቤቱ የአሰራር መመሪያ የሌላቸው የሥራ ሂደቶች መኖራቸው፣
- ከተገልጋይ ጋር መገናኘት የሌለባቸው የላቦራቶሪ ባለሙያዎች በቀጥታ ከተገልጋይ ጋር የሚገናኙ መሆኑ፣
- መ/ቤቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚስከፍለው ክፍያ ተመን በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ እና በተመኑ መሰረትም ክፍያ የማይሰበሰብ መሆኑ፣ ክፍያውም ላይ ክለሳ ተደርጎ የማያውቅ መሆኑ፣
- ለምርመራ የሚመጡ ናሙናዎችን አያያዝ በተመለከተ መመሪያ አለመኖሩ፣ ለምርመራ የመጡ ናሙናዎች ለባለቤቶቻቸው ሳይመለሱ ወይም ሳይወገዱ በመጋዘን ለረጅም ዓመታት ተጠራቅመው የሚገኙ መሆናቸው፣
- የተለያዩ ንብረቶችና ኬሚካሎች መወገድ የሚገባቸው ሆኖ ሳለ ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የሚያገለግሉ የድሪሊንግ እና የላቦራቶሪ ማሽኖች ያለአገልግሎት በመጋዘን ለረጅም አመታት የተቀመጡ መሆናቸው፣

- ተጠግነው ስራ ሊሰሩ የሚችሉ ንብረቶች በሜዳ ላይ ተቀምጠው ለበለጠ ጉዳት እየተዳረጉ የሚገኙ መሆኑ፣
- ናሙናዎች ለተጠቃሚ አመቺ በሆነበት መልኩ አለመደራጀታቸው እና በአመት ሁለት ጊዜ መከናወን የነበረበት ለኮርና ለአለት ናሙናዎች ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ፣
- መ/ቤቱ በተዘጋጀው የስትራቴጂክ ሆነ ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ስራውን የማይከናወን መሆኑ፣
- በመ/ቤቱ የስነ ምድር መረጃዎች ከተለያዩ ተቋማት በእቅድ ላይ በተመሰረተ፣ ወጥ በሆነ እና በተደራጀ መልኩ በመሰብሰብ ለተገልጋይ ዝግጁ የማይደረግ መሆኑ፣
- መ/ቤቱ የተገልጋዮችን /ባለድርሻዎችን እርካታ የሚያሳይ ደሰሳ ጥናት አለማድረጉ፣
- በመ/ቤቱ የሚሰጡ ስልጠናዎች ውጤታማነት ላይ ግምገማ አለመደረጉ እና ዕኩል የስልጠና ስርጭት አለመኖሩ፣
- በመ/ቤቱ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- መ/ቤቱ በማዕድን ፍለጋ፣ በድሪሊንግ እና በላቦራቶሪ የሚሰሩ ሰራተኞችን በተለይም የሴት ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ምቹ የሥራ አካባቢ አለመኖሩ እና ጥራት ያላቸዉ የሴፍቲ እቃዎች በተሟላ መልኩ አለማቅረቡ፣

ታውቋል፡፡

77. በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

78. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የማዕድን ፍለጋ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲያከናወንና ጥራት ያለው መረጃ ለተገልጋዮች እንዲያቀርብ፣ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ ለማስቻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም በቀጣይ በሚከናወኑ የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- በመ/ቤቱ የተለያዩ የላቦራቶሪ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የተገዙ ማሽኖችና ኬሚካሎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና መጠገን የሚገባቸውንም በአፋጣኝ ጥገና እንዲደረግላቸው በማድረግ የጥራት ማረጋገጥ ስራ ሊሰራ እና ሌሎች ላቦራቶሪው ላይ መስተካከል ያለባቸውን ክፍተቶች በማስተካከል ተገቢውን ቀልጣፋ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከ10 ዓመት በፊት የተጀመረው የመ/ቤቱ ላቦራቶሪ አለምአቀፍ ዕውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ የጀመረውን ዕቅድ በፍጥነት ወደ ተግባር በማሸጋገር ወደ ውጭ የሚላኩ የማዕድን ናሙና ምርመራዎችን በመስራት ወደ ውጭ የሚላከውን የምርመራ መጠን ሊቀነስና ለምርመራ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ የሚቀነስበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም እያደገ ለመጣው የማዕድን ዘርፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለመወጣት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- መስሪያ ቤቱ ተግባሩን ለማከናወን የሚጠቀምባቸው የቁፋሮ (ድሪሊንግ)፣ የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች ለብልሽት እንዳይዳረጉ ቅድመ መከላከል ሥራ ለመስራት የሚያስችል የመደበኛ ጥገና ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ዕቃዎች ከውጭ በሚገዙበት ወቅት ጥገናቸውን በተመለከተ ከግዥው ጋር እንዲካተት ቢደረግ የተሻለ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የመለኪያ አገልግሎት የሚሰጡ የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ የማዕድን ቁፋሮ መሳሪያዎችና የተለያዩ ማሽኖች በየአመቱ ትክክል ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ካሊብሬት ሊደረጉ እንዲሁም ካሊብሬት በሚደረግበት ወቅት መርሃ ግብርን መሰረት ያደረገና ተከታታነት ያለዉ ባለመሆኑ በዚህ መልኩ መከናወን ይኖርበታል፡፡

- ለቁፋሮ (ለድሪሊንግ)፣ ለላቦራቶሪ እና ለጂኦሳይንስ መረጃ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢን በተመለከተ ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር እና ለተገልጋዮች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ወቅታዊ የክፍያ መመሪያ ሊዘጋጅ እና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ወደ ተግባር ሊገቡ ይገባል፡፡ እንዲሁም መመሪያ የተዘጋጀላቸው ክፍሎች ላይ ክትትል በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲሰሩ ሊደረግ እና የአሰራር መመሪያ ለሌላቸው ክፍሎች አዋጁን መሰረት በማድረግ መመሪያ ሊዘጋጅላቸውና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ወደ ተግባር የሚገባበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡
- በመ/ቤቱ ለምርመራ የሚመጡ ናሙናዎችን በአግባቡ ለመያዝና ምርመራቸው ተከናውኖ ካለቀ በኋላም ናሙናዎቹ ለባለቤቶቹ የሚመለሱበትን ወይንም የሚወሰዱበትን የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ለረጅም አመታት የተከማቹ ናሙናዎችን የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት ጊዜያቸው በማብቃቱ ተጠግነው ስራ ላይ የማይውሉና ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ንብረቶች ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በአገር ውስጥ አይወገዱም የተባሉትን ኬሚካሎችም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባባር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሚወገዱበትን ሁኔታ በማመቻቸት እንዲወገዱ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በመ/ቤቱ እና ከተለያዩ ድርጅቶች በየጊዜው የሚሰበሰበውን የኮርና የአለት ናሙና ለተጠቃሚዎች አመቺ በሆነ ሁኔታ ሊመዘግብ፣ ናሙናዎቹም ሥርዓት ባለው መንገድ ተይዘው ለተጠቃሚዎችና ለተመራማሪዎች ሊታዩ በሚችል አግባብ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የኮርና አለት ናሙናዎች በመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ጥናት ላይ በተቀመጠው መሰረት በአመት ሁለት ጊዜ ቆጠራ ሊካሄድባቸው እና ሰነዶቹም በአግባቡ የሚቀመጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ የቁፋሮ አገልግሎት ለመስጠት ከደንበኞቹ ጋር የሚገባውን ውል የሚያስፈልገውን ግብዓት ቅድሚያ በማሟላት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብና ጥራት በማከናወን ውሉን ሊፈጽም ይገባል፡፤ በውሉ መሰረት ባለማከናወን ሊከሰት ለሚችል አላስፈላጊ ጉዳት የካሳ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ሊያደርግና መንግስትን

አላስፈላጊ ከሆነ ወጪ ማዳን ያለበት ሲሆን የመ/ቤቱም መልካም ስም እንዳይጎድፍ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለመወጣት እንዲያስችለው በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ በመመስረት ስራዎችን ሊያከናውን ይገባል፤ ዕቅድ በሚታቀድበትም ጊዜ ያለፉ አመታትን ዕቅድ አፈፃፀም በማገናዘብና መሰረት በማድረግ የቀጣይ አመታትን ዕቅድ ሊያዘጋጅ የሚገባ ሲሆን አፈፃፀሙንም በተመለከተ በዕቅዱ መሰረት እንዲከናወን በትኩረት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ የሚያከናውናቸዉ ስራዎች ለሀገሪቱ የማዕድን ኢንቨስትመንት እድገት ወሳኝ ሚና ያላቸዉ በመሆኑ ለተገልጋዮች ጥራት ያለው መረጃ በተሟላ መልኩ ለማቅረብ እንዲቻል ዕቅድን መሰረት በማድረግ የስነ-ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት መሰብሰብና ማደራጀት እንዲሁም በመ/ቤቱ ያሉ መረጃዎችን መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱን መሰረት በማድረግ ማደራጀትና የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማስተዋወቅ ይገባዋል፡፡ ይህንን በማድረግ መ/ቤቱ ጠቃሚ መረጃዎችን በማቅረብ ለሀገሪቱ የማዕድን ኢንቨስትመንት እድገት የራሱን ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ በሚያከናዉናቸዉ የማዕድን ፍለጋ ጥናት መረጃዎች ተገልጋዮች ያገኙትን ጥቅም ለመረዳት እንዲሁም ክፍተቶችን ለመለየትና ለመሙላት እንዲቻል የተገልጋዮችን/ የባለድርሻዎችን እርካታ የሚያሳይ የደሰሳ ጥናት ሊያከናውን በጥናቱ መሰረትም የማስተካከያ እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከተገልጋዮች የአገልግሎት አሰጣጥ ግብረ መልስ የሚያገኝበትን እና የውጭ ተገልጋዮች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- መ/ቤቱ ስልጠናዎችን በዕቅድ በማካተት ሰራተኛውን ያሳተፈ እና ለሚመለከተዉ አካል የሚመለከተዉን ስልጠና በመስጠት ስራዎች ለተገልጋይ ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም ስልጠናው ያመጣውን ውጤት መገምገም ይኖርበታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መ/ቤቱ በቁፋሮ (ድሪሊንግ)፣ በማዕድን ፍለጋ ግምትና ክምችት እና በላቦራቶሪ የሚሰሩ ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ ምቹ የሥራ አካባቢ ሊፈጥር እና ጥራት ያላቸዉ የደህንነት መሳሪያዎችን በወቅቱ ማቅረብ እንዲሁም የስራ ላይ ደህንነትን እና መሳሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ የተለያዩ የስልጠና

መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤ መፍጠር ይኖርበታል፡፡ በተለይም በመ/ቤቱ በማዕድን ፍለጋ ግምትና ክምችት፣ በላቦራቶሪና በቁፋሮ (ድሪሊንግ) የሚሰሩ ሴት ሰራተኞች ላይ ትኩረት በማድረግ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በሚያስችል መልኩ ዕቅድ በማቀድና ተግባራዊ በማድረግ በስራ ቦታ ከሚደርስ የደህንነት ስጋት እንዲወጡ የሚያደርግ አሰራር ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡


በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል መ/ቤቶች እና የማዕድን ኩባንያዎች ለሚገኙ የበላይ ሀላፊዎችና ሰራተኞች በሙሉ ስለተደረገልን ቀና የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡- መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria's)

| የኦዲት ጭብጥና (Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| የማዕድን ፍለጋ ብቃት ያለው ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑ ማረጋገጥ፤ | 1. የተለያዩ የማዕድን ፍለጋ ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም መርሀ ግብር ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት የስራ ሂደት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ገፅ 43፣ 38)* |
| | 2. የማዕድን ፍለጋ ፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም በመርሀ ግብሩ መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት የስራ ሂደት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ገፅ 43፣ 38)* |
| | 3. ለቁፋሮ፣ ለላቦራቶሪ እና ለጂኦሳይንስ መረጃ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢን በተመለከተ የተዘጋጀ የክፍያ መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (አዋጅ ቁጥር 194/1992)* |
| | 4. የቁፋሮና የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡ ዕቃዎች በትክክል አገልግሎት እንደሚሰጡ መደበኛ የጥገናና የፍተሻ (ካሊብሬሽንን ጨምሮ) ሊከናወንላቸው ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (የ2003-2007 ዓ/ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 53 ፤ የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና ክብካቤ ገፅ 64 እና Standared Procedures for examination of different geological materials central geological laboratory ገፅ 137፣75)* |
| | 5. ወደ ውጪ የሚላኩ እና በሀገር ውስጥ የሚከናወኑ የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራዎችን መረጃ ተሰብስቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (2003-2007 ዓ/ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 53)* |
| | 6. ለተገልጋዮች የሚሰጠው የቁፋሮ (የድሪሊንግ) እና የላቦራቶሪ አገልግሎት የአሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (ልሳነ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ቅፅ 8 ቁጥር 10 ነሀሴ 2008 ዓ/ም)* |
| | 7. በየጊዜው የሚሰበሰበውን የኮርና የአለት ናሙና በዳታ ቤዝ በማስገባት በአመት ሁለት ጊዜ ቆጠራ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (የጂኦሳይንስ መረጃ ማዕከል መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ገፅ 11)* |
| | 8. በእያንዳንዱ የላቦራቶሪ ምርመራ ደረጃ ላይ በሚመለከተው በመረመረው አካል/ባለሙያ ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ አሰራር መመሪያ ገፅ 10* |
| | 9. የናሙና አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ አሰራር መመሪያ ገፅ 5፣ 14* |
| | 10. አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተውና በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (መልካም ተሞክሮ)* |
| | 11. በመ/ቤቱ ያሉ ያገለግሉ እና መወገድ የሚገባቸው የቁፋሮና እና የላቦራቶሪ ማሽኖች፣ ኬሚካሎች እና ናሙናዎች በየጊዜው የሚወገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና ክብካቤ ገፅ 37 እና መልካም ተሞክሮ)* |
| መረጃ አያያዝ፣ አሰጣጥና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸው | 12. የስነ ምድር መረጃዎችን ከተለያዩ ተቋማት ለመሰብሰብና ለተገልጋይ ዝግጁ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊኖርና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- (አዋጅ ቁጥር 194/1992፣ 2003-2007 ዓ/ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 40 እና የጂኦሳይንስ መረጃ ማዕከል የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሪፖርት ገፅ 41)* |

| | |
|---|---|
| **ቅንጅታዊ አሰራር መገምገም፤** | 13. መ/ቤቱ ስለሚያከናውናቸው ስራዎችና የአገሪቱን የጂኦሳይንስ መረጃዎች በተመለከተ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማስተዋወቅ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (አዋጅ ቁጥር 194/1992፣ የጂኦሳይንስ መረጃ ማዕከል የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሪፖርት ገፅ 42 እና ከ2003-2007 ዓ/ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 40፣ 51)* |
| | 14. መ/ቤቱ የስነ ምድር መረጃ ለማደራጀት እና ለማሰራጨት ዘመናዊ መረጃ አጠቃቀም ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት ቢፒአር ገፅ 50፣ 93፣ 94፤ የ2003-2007 ዓ/ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 40 እና የጂኦሳይንስ መረጃ ማዕከል የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሪፖርት ገፅ 42)* |
| | 15. መ/ቤቱ በማዕድን ፍለጋ፣ በላቦራቶሪ፣ በቁፋሮ (ድሪሊንግ) እና ጂኦሳይንስ መረጃ ላይ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በዕቅድ የተደገፈ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት የስራ ሂደት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ገፅ 89፣ 90 እና አዋጅ ቁጥር 194/1992)* |
| | 16. ላቦራቶሪ የሚሰጠው አገልግሎት የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ያሟላ እንዲሆን የጥራት ቁጥጥር ሊኖር ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (2003-2007 ዓ/ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 43 እና Standard Procedures for examination of different geological materials central geological laboratory ገፅ 6)* |
| | 17. መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸውን የድሪሊንግና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች በፍጥነት ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ የሚያስችል አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (Drilling BPR ገፅ 65 እና የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስናና ጥገና ክብካቤ ቢፒአር ገፅ 20)* |
| | 18. መ/ቤቱ የተገልጋዮችን/ የባለድርሻዎችን እርካታ የሚያሳይ የደሰሳ ጥናት ሊያከናውን ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት የስራ ሂደት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ገፅ 43፣ 52፣ 54)* |
| | 19. የተገልጋዮች ቅሬታ አፈታት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (መልካም ተሞክሮ እና የጂኦሳይንስ ላቦራቶሪ አሰራር መመሪያ ገፅ 16)* |
| | 20. በመ/ቤቱ ቁፋሮ (Drilling)፣ በማዕድን ፍለጋ እና በላቦራቶሪ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ደህንነት ሊጠበቅ የሚችልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (የሳይንቲፊክ መሳሪያዎች ምህንድስና፣ ጥገናና ክብካቤ ገፅ 29)* |
| | 21. በማዕድን ፍለጋ፣ በላቦራቶሪ እና በቁፋሮ (ድሪሊንግ) ላይ የሚሰሩ ሴት ሰራተኞችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸውን እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (መልካም ተሞክሮ)* |
| | 22. በመ/ቤቱ የሚሰጠው የላቦራቶሪ አገልግሎት በገለልተኛ አካል ሊገመገም ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (መልካም ተሞክሮ)* |
| | 23. በመ/ቤቱ የሚገኙ የድሪሊንግ፣ የላቦራቶሪ እና የማዕድን ፍለጋ ንብረቶችን በአግባቡ ለመያዝና ለመጠቀም የሚያስችል የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡- (መልካም ተሞክሮ)* |

# አባሪ 2፡- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 3፡- የዕቅድ አፈፃፀሞች ከመቶ ፐርሰንት በላይ መሆናቸውን ለማሳየት

| ስራው የተከናወነበት ዘርፍ | በመ/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራት | ዕቅድ | ዕቅድ አፈፃፀም | በመቶ ኛ |
|---|---|---|---|---|
| የተለያዩ ስልጠናዎች | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የትምህርት እና ስልጠና መስጠት በቁጥር | 470 | 980 | 208.5 % |
| | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ተቋማት ስልጠና መስጠት በቁጥር | 80 | 132 | 165% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በመስሪያ ቤቱ ስልጠና መስጠት በቁጥር | 200 | 665 | 332.5 % |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ተቋማት ስልጠና መስጠት በቁጥር | 60 | 98 | 163.33 % |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ከሀገር ውጪ ስልጠና መስጠት በቁጥር | 10 | 25 | 250% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት በቁጥር | 250 | 345 | 138% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ተቋማት ስልጠና መስጠት በቁጥር | 60 | 139 | 231.66 % |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ከሀገር ውጪ ስልጠና መስጠት በቁጥር | 18 | 40 | 222.22 % |
| የማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምት ጥናት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ማዕድን ፍለጋና ልማት ልማት ፕሮጀክት | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የስትሪም ሴድመንት ናሙና መሰብሰብ በቁጥር | 318 | 1864 | 586% |
| | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የጂኦኬሚካል አፈር ናሙና መሰብሰብ በቁጥር | 10,000 | 10,164 | 102% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የጂኦኬሚካል አፈር ናሙና በቁጥር | 2000 | 3250 | 163% |
| የኢንደስትሪ ማዕድናት ፍለጋና ጥናትን በተመለከተ፡- | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የጂኦሎጂ ካርታ ሥራ በ1፡10000-1፡20000 መስፈርት ማከናወን | 30 ካ.ኪ.ሜ | 30 ካ.ኪ.ሜ | |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሴክሽን ሎጊንግ ማከናወን | 100 መ. | 110 መ.ሜ. | 110% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ሜ. | | |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የጂኦሎጂ ካርታ ሥራ በ1፡10000-1፡20000 መስፈርት ማከናወን | 30 ካ.ኪ. ሜ | 780 ካ.ኪ.ሜ | 2600% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሴክሽን ሎጊንግ ማከናወን | 100 መ.ሜ. | 150 መ.ሜ | 150% |
| የጀምስቶን ማዕድን ፍለጋ ጥናትን በተመለከተ | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የተለያዩ የጀምስቶንና አለት ናሙናዎች መሰብበሰብ በቁጥር | 100 | 225 | 225% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የዝርግ ጉድጓድ/ፒት ቁፋሮ ማከናወን | 50 መ.ሜ. | 82 መ.ሜ. | 164% |
| የጂኦሳይንስ መረጃን በተመለከተ፡- | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የጂኦሳይንስ መረጃዎች ወደ ሰርቬዩ መረጃ ማዕከል ማሰባበሰብና ማደራጀት | 90 | 120 | 133% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የጂኦሳይንስ መረጃዎች ወደ ሰርቬዩ መረጃ ማዕከል ማሰባበሰብና ማደራጀት | 100 | 118 | 118% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም አዲስ ወደ ቤተ መፅሀፍት የሚገቡ ህትመቶችን ክላሲፋይና ካታሎግ በማድረግ ማደራጀት | 90 | 120 | 133% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም አዲስ ወደ ቤተ መፅሀፍት የሚገቡ ህትመቶችን ክላሲፋይና ካታሎግ በማድረግ ማደራጀት | 100 | 118 | 118% |
| በኦጋዴን ቤዚን የመሰረታዊ የጂኦሳይንስ ካርታ ዝግጅትን በተመለከተ፡- | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በመስክ የግራቪቲ መረጃ መሰብሰብ | 2005 መ.ኪ .ሜ. | 2005 መ.ኪ.ሜ. | 100% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በመስክ የግራቪቲ መረጃ መሰብሰብ | 1295 መ.ኪ .ሜ | 1295 መ.ኪ.ሜ | 100% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በመስክ የግራቪቲ መረጃ መሰብሰብ | 1200 መ.ኪ .ሜ | 1200 መ.ኪ.ሜ. | 100% |

## አባሪ 4፡ ዕቅድ አፈፃፀሞች ዝቅተኛ እና ያልተከናወኑ መሆናቸውን ለማሳየት

| ስራው የተከናወነበት ዘርፍ | በመ/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራት | ዕቅድ | ዕቅድ አፈፃፀም | በመቶ ኛ |
|---|---|---|---|---|
| የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ማዕድን ፍለጋና ልማት ፕሮጀክትን በተመከለተ፡- | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም 1፡250000 መስፈርት የተዘጋጀውን የጂኦሎጂ ካርታ በመጠቀም በመስክ የማረጋገጫ የጂኦሎጂ ጥናት ማካሄድ | 3144 ካ.ኪ.ሜ. | 100 ካ.ኪ.ሜ. | 3% |
| | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በ1፡250000 መስፈርት የጂኦኬሚካል ሰርቬይ ማካሄድ | 6060 ካ.ኪ.ሜ. | 1864 ካ.ኪ.ሜ. | 31% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በ1፡250000 መስፈርት የጂኦኬሚካል ሰርቬይ ማካሄድ | 4196 ካ.ኪ.ሜ. | 1052 ካ.ኪ.ሜ. | 25% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በ1፡250000 መስፈርት የጂኦኬሚካል ሰርቬይ ማካሄድ | 3144 ካ.ኪ.ሜ. | 80 ካ.ኪ.ሜ. | 3% |
| | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በ1፡10000 መስፈርት የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪ እና የጂኦፊዚክስ ስራዎች የሚሰሩባቸው ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀት | 1000 መ.ኪ.ሜ. | 427 መ.ኪ.ሜ. | 43% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በ1፡250000 መስፈርት የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪ እና የጂኦፊዚክስ ስራዎች የሚሰሩባቸው ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀት | 2100 መ.ኪ.ሜ. | 237 መ.ኪ.ሜ. | 11% |
| | በ2007 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በ1፡10000 መስፈርት የጂኦፊዚክስ ካርታ ስራ ማከናወን | 400 ካ.ኪ.ሜ | 90 ካ.ኪ.ሜ | 23% |
| | በ2007 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የዝርግ ጉድጓድ (ፒት ቁፋሮ) ማከናወን | 8000 ሜትር ኪዩብ | 3000 ሜትር ኪዩብ | 3 8% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ሄቪ ኮንሰንትሬሽን ናሙና መሰብሰብ በቁጥር | 935 | 250 | 27% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የሜታሊክስ ማዕድናት (የደለል ወርቅ) ፍለጋና ጥናትን በተመለከተ፡- | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም የደለል ወርቅ የአለኝታ ቦታዎች የጥናት ውጤት በክልል ለተደራጁ የወርቅ አምራች ማህበራት ማቅረብ በቁጥር | 15 | 7 | 46% |
| | በ2009 በጀት አመት አፈፃፀም የደለል ወርቅ የአለኝታ ቦታዎች የጥናት ውጤት በክልል ለተደራጁ የወርቅ አምራች ማህበራት ማቅረብ በቁጥር | 21 | 9 | 42% |
| የመስክ ሪፖርትን በተመለከተ፡- | በ2007 ዓ.ም በኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍለጋ ጥናት ፕሮጀክት የድህረ መሰክ ሪፖረትና ካርታ ዝግጅት ማከናወን | 10% | 2% | 20% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርት ላይ በማዕድን ፍለጋና ክምችት ግምገማ ጥናት ስር የሚከናወኑት የሜታሊክ (የደለል ወርቅ) ፍለጋና ጥናት፣ የኢንደስትሪ ማዕድናት እና ካርታ ዝግጅት እንዲሁም የድንጋይ ከሰልና ኦይል ሼል ፍለጋና ጥናት የድህረ መስክ ስራ የማጠቃለያ ሪፖርት ዝግጅት | 100% | - | - |
| ላቦራቶሪን በተመለከተ፡- | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በጀኦኬሚካል ላቦራቶሪ የወርቅ ባር ምርመራ በሸሬ | | | 45% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በጀኦኬሚካል ላቦራቶሪ የወርቅ ባር ምርመራ በሀዋሳ | | | 12% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም በጀኦኬሚካል ላቦራቶሪ የወርቅ ባር ምርመራ በአሶሳ፣ በሀዋሳ፣ በሚዛን አማን፣ በሽሬ እና በሻኪሶ በቅደም ተከተላቸው የተጠቀሰው አፈፃፀም ብቻ መሆኑ | | | 45%፣ 4%፣ 46%፣ 41%፣ 12% |
| | በ2007 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም የሚኒራሎጂና ፔትሮግራፊ ምርመራ ናሙናዎች ማከናወን በቁጥር | 77901 | 2775 | 36% |
| | በ2007 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም በጂኦሳይንስ ላብራቶሪ ላይ የዉሃ ናሙናዎች ምርመራ ማከናወን በቁጥር | 3491 | 1575 | 45% |
| | በ2007 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም የፊዚካል ምርመራ ማከናወን | 2527 | 874 | 35% |
| | በ2009 በጀት አመት አፈፃፀም ሪፖርት ላይ | 53632 | 13911 | 26% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ለሰርቬዩና ለውጭ ተገልጋዮች ናሙናዎች ምርመራ ማከናወን በቁጥር | | | |
| | • በ2007 እና 2008 በጀት አመት ለላቦራቶሪው የምርመራ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን የሚያቀርቡ አቅራቢዎችን (Short List) ማድረግ<br>• እንዲሁም በቀጣዩ አመት 2009 በዕቅድ ላይ ያልተካተተ መሆኑን | 100% | - | - |
| ድሪሊንግን በተመለከተ፡- | በ2007 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በድሪሊንግ አገልግሎት የኮር ድሪሊንግ ጂኦቴክኒክ ስራ ለማከናወን | 5000 ሜትር | 1371.55 | 27% |
| | በ2007 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የዉሃ ድሪሊንግ ስራ ማከናወን | 3000 ሜትር | 173 ሜትር | 6% |
| | በ2007 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የጂኦተርማል ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ማከናወን | 10000 ሜትር | 1920 ሜትር | 20% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የኮር ድሪሊንግና የጂኦቴክኒክ ስራ ማከናወን | 7000 ሜትር | 3257 ሜትር | 47% |
| | የጂኦተርማል ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ማከናወን | 10000 ሜትር | 1951 ሜትር | 20% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ውሃ ድሪሊንግ ስራ ማከናወን | 3000 ሜትር | 138.4 | 5% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የኮር ድሪሊንግና የጂኦቴክኒክ ስራ ማከናወን | 5000 ሜትር | 919 ሜትር | 18.3% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የውሃ ድሪሊንግ ስራ ማከናወን | 7000 ሜትር | 201.05 ሜትር | 3% |
| ሌሎች ዕቅድ አፈፃፀሞችን በተመለከተ፡- | በ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የብረት ማዕድን ፍለጋና ጥናት ላይ የጂኦፊዚክስ ስራዎች ማከናወን | 200 መ.ኪ.ሜ | 35 መ.ኪ.ሜ | 18% |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈጻፀም የብረት ማዕድን ፍለጋና ጥናት ላይ የጂኦፊዚክስ ስራዎች ማከናወን ታቅዶ ያልተከናወነ | | - | - |
| | በ2007 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የሂቪ ኮንሰንትሬት ናሙና መሰብሰብ በቁጥር | 500 | 200 | 40% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የጂኦሎጂ ካርታ ሰርቬይ በ1፥50000-1፥10000 መስፈርት ማከናወን | 500 ካ.ኪ.ሜ. | 137 ካ.ኪ.ሜ | 27% |
| | በ2008 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የዝርግ ጉድጓድ (ፒት) ቁፋሮ ማከናወን | 2000 ሜ.ኪዩብ | - | - |
| | በ2009 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ በማዕድን ፍለጋና ክምችት በብረት ፍለጋና ጥናት የጂኦፊዚክስ ስራዎች እንዲሁም የዝርግ ጉድጓድ /ፒቲ ቁፋሮ ማከናወን | 100 መ.ኪሜ እና 200 መ.ሜ | - | - |